# ረቂቅ የንግድ ሕግ አጭር ማብራሪያ

2012 ዓ/ም

# 1. መግቢያ (በአጠቃላይ ስለንግድ ዳራ)

## 1.1 የንግድ ሕግ ዓላማዎች

አንድ ግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማኅበር በዕለት ተዕለት የንግድ እንቅስቃሴው ከተለያዩ አካላት ጋር የውል እና ከውል ውጪ የሆኑ ግንኙነቶችን ይፈጥራል። ለምሳሌ፡- አንድ የንግድ ድርጅት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች ከሚያቀርቡ ድርጅቶች፣ ምርቶቹን እና አገልግሎቶቹን ከሚገዙት ደንበኞች ወይም ሸማቾች፣ ለድርጅቱ ብድር ከሰጡ ወይም በሌላ ምክንያት ከድርጅቱ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ካላቸው ሰዎች፣ ከንግድ ተወዳዳሪዎቹ፣ ከተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እንዲሁም ከድርጅቱ ሠራተኞችና ሥራ አመራሮች ጋር ግንኙነት ይኖረዋል፤ ድርጅቱ ከባለሀብቶቹ የተለየ የራሱ የሕግ ሰውነት ያለው የንግድ ማኅበር ሲሆን ደግሞ ከማኅበርተኞቹ ጭምር ግንኙነት ይኖረዋል።

ከላይ ከተገለጹት የንግድ ድርጅት ከሚፈጥራቸው ዘርፈ ብዙ ግንኙነት አኳያ የንግድ ሕጎች ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች አሏቸው፡- አንደኛው ዋና ዓላማ አንድ የንግድ ድርጅት ከላይ በተመለከትናቸው ውስብስብ ግንኙነቶች ውስጥ ተንቀሳቅሶ ሀብት እንዲያፈራ እና አትራፊ እንዲሆን የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማበጀት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከላይ ለተጠቀሱት ከአንድ የንግድ ድርጅት ጋር የተለያዩ ግንኙነቶች ለሚፈጥሩት አካላት መብቶች እና ቅቡልነት ያላቸው ፍላጎቶች ተገቢውን የሕግ ጥበቃ ማድረግ ነው። የንግድ ሕግ መድብል (ኮድ) እነዚህን ሁለት አንኳር ዓላማዎች ይጋራል።

ይህ ሲባል ግን የንግድ ሕግ መድብል (ኮድ) ሁሉንም ከላይ የተመለከትናቸውን ግንኙነቶች አሟልቶ ይገዛል ማለት አይደለም። ለምሳሌ፡- የንግድ ድርጅት ከሠራተኞቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ ይገዛል። በተመሳሳይ ሁኔታ የግብር እና ጉምሩክ ጉዳዮች እነዚህን አስመልክተው በወጡ ልዩ ሕጎች፣ የንግድ ድርጅት ከተፎካካሪዎቹ የሚኖረው ግንኙነት የንግድ ምልክቶችን፣ የንግድ ስሞችን፣ ፓተንትን እና መሰል መብቶችን በሚገዙ ሕጎች ወዘተ ሊገዙ ይችላሉ። ባጭሩ በተለየ ባህሪያቸው ምክንያት ዝርዝር ሕግ እና የተለየ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ያላቸው ከንግድ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሕጎች ከንግድ ሕግ መድብል/ኮድ/ ውጪ ሊኖሩ አይችሉም ማለት አይደለም። ከንግድ ጋር ንክኪ ያላቸውን ሕጎች በሙሉ በአንድ መድብል/ኮድ/ ለማካተት መሞከር ጠቀሜታውም ሆነ ተግባራዊነቱ እጅግ አጠያያቂ ነው፤ የሌሎችን አገራት ልምድም ስንመለከት የንግድ መድብሉ/ኮድ/ የንግድ ድርጅት መተዳደሪያ መሠረታዊ ድንጋጌዎች የሚያስቀምጥ ሲሆን ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ደግሞ በተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች የሚካተቱ ይሆናሉ።

በ1952 የወጣውን የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መድብል (ኮድ) ያካተታቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት አንድ የንግድ ድርጅት በኢኮኖሚ እንቅስቃሴው የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶችን በሙሉ ለመግዛት አይሞክርም። ኮዱ በዋናነት ከአንድ የንግድ ድርጅት ገንዘብ የመጠየቅ መብት ላላቸው ሰዎች ስለሚደረግ የሕግ ጥበቃ፣ በንግድ ማኅበር አባላት መካከል ስለሚኖረው የእርስ በርስ ግንኙነት፣ በንግድ ማኅበር እና በአባላቶቹ መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት፣ በንግድ ድርጅት እና በሥራ አመራሩ መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት ድንጋጌዎችን ይዟል። በተጨማሪም የ1952ቱ የንግድ ሕግ በልዩ ሁኔታ በባንክ እና መድን ሥራዎች የተሰማሩ የንግድ ድርጅቶች ከደንበኞቻቸው ጋር ያላቸውን የውል ግንኙነት የሚገዙ ሕጎች አካቷል። የንግድ ሕጋችን የሸፈናቸው ጉዳዮች ብዛት መነሻ ካደረጋቸው የምዕራብ አውሮጳ እናት ሕጎች የሰፋ ነው ሊባል ይችላል። ይህ የሆነው የንግድ ሕጉ በወጣበት ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የሚገዙ ሕጎች በጣት የሚቆጠሩና ያልተሟሉ

እንደነበረ ለመገመት ይቻላል፤ ነበሩ የሚባሉትም ቢሆኑ ሕጎች ይሁኑ የሕግ ረቂቆች ግልጽ አልነበረም።[1] በመሆኑም የንግድ ሕጉን ያረቀቁት ሰዎች የነበረውን እጅግ ሰፊ የሕግ ክፍተት ለመድፈን የተለያዩ ጉዳዮችን በስሱ የሚሸፍኑ ቅንጭብጫቢ ድንጋጌዎችን በንግድ ሕጉ ውስጥ ለማካተት የተገደዱበት ሁኔታ መኖሩን ማስተዋል ይቻላል።[2]

በሌላ በኩል የንግድ ሕጉ በዝምታ ያለፋቸው ብዙ ከንግድ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ ለንግድ ድርጅቶች የሥራ ፈቃድ ስለሚሰጥባቸው መመዘኛዎች፣ የንግድ ድርጅቶች መከተል ስለሚገባቸው የማምረት እና አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት፣ ስለሚያመርቱት ምርት ደረጃ፣ ስለሚሰጡት የአገልግሎት ጥራት እና በመንግሥት ስለሚደረግባቸው ቁጥጥር በኮዱ አልተካተቱም፤ እንዲህ ዓይነቶቹን ከንግድ ሥራ ጋር ቁርኝት ያላቸው ጉዳዮች የመግዛት ዓላማ የለውም። እነዚህ የቁጥጥር ወይም አስተዳደራዊ (regulatory) ባሕሪ ያላቸው ጉዳዮች በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከሚሳተፉት ተዋንያን ባህሪ፣ የገበያ ሁናቴ፣ ከአስተዳደር አካላት አደረጃጀት እና አቅም ወዘተ አንጻር በየጊዜው በቀላሉ መለወጥ መቻል አለባቸው። በመሆኑም እነዚህ እና መሰል አስተዳደራዊ ጉዳዮች በየጊዜው በሚወጡ ሌሎች ሕጎች አንጂ በሕግ መድብል ኮድ የሚወሰኑ አይደሉም።

## 1.2 የ1952ቱ የንግድ ሕግ ታሪካዊ ዳራ

በ1952 ዓ.ም ወጥቶ ዛሬ ድረስ ሥራ ላይ የሚገኘውን የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ በአብዛኛው ያረቀቁት በፓሪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር እና የፈረንሳይ የንግድ ሕግ ክለሳ ኮሚሽን ሊቀመንበር የነበሩት ጆአን ኤስካራ ነበሩ። ሆኖም እሳቸው ረቂቁን ሳያገባድዱ በመሞታቸው ቀሪውን ሥራ ሌላ ፈረንሳዊ ፕሮፌሰር አልፍሬድ ጆፍሬ ማገባደዳቸው ይታወቃል።

ፕሮፌሰር ኤስካራ ሥራቸውን ሲጀምሩ የንግድ ሕጉን የሲቪል ሕግ ሥርዓት የሚከተሉትን የምዕራብ አውሮጳ አገሮች ሕጎች ~~መሰረት አድርገው እንዲያረቁ በኢትዮጵያ~~ መንግሥት የሥራ መመሪያ እንደተሰጣቸው ይገልጻሉ።[3] በመሆኑም የንግድ ሕጋችን የወጣው በዋናነት የንግድ ሕግ በመድብል/ኮድ/ መልክ ለመጀመሪያ ጊዜ ያወጣችው የፈረንሳይ ሕግ እና የዚሁ ሕግ ተጽዕኖ በስፋት የሚንጸባረቅባቸው የሌሎች አገሮች ሕጎችን መሰረት በማድረግ ነበር። በተጨማሪም አርቃቂዎቹ የፈረንሳይ የንግድ ኮድ ከወጣ ከመቶ ዓመት በኋላ ከፍተኛ ተጽዕኖ በመፍጠር ላይ የነበረውን የጀርመን የንግድ ሕግና ተሞክሮ በሰፊው ዳስሰዋል። አልፎ ተርፎም በዘመኑ አዲስ የነበሩትን የሊባኖስ እና የሶሪያ ሕጎችን ጨምረው የተለያዩ የሲቪል የሕግ ሥሥርዓት የሚከተሉ አገሮች ሕጎችን በማየት  ጥሩ ያሏቸውን የሕግ ጽንሰ ሐሳቦች እና ድንጋጌዎች በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ ለማካተት መሞከራቸውን ፕሮፌሰር ኤስካራ ይገልጻሉ።

ሕጉ በተረቀቀበት ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ ውሱን የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ እና ልማድ ነበረ፤ በጣት የሚቆጠሩም ቢሆን ንግድ ነክ ሕጎች እና አሰራሮችም ነበሩ። በመሆኑም አርቃቂው መሬት ላይ የነበረውን እውነታ ግምት ውስጥ ማስገባት ነበረባቸው። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ውስጥ እንግሊዛዊያን ዳኞች እና ባለሞያዎች በነበረቸው የጎላ ሚና የተነሳ የእንግሊዝን የሕግ ሥርዓት መሰረት ያደረጉ አንዳደንድ ሕጎች፣ አሰራሮች፣ ልምዶች እና የፍርድ

---

[1] Peter Winship, Background Documents of the Ethiopian Commercial Code of 1960 (Haileselassie I University 1974) p.14 to 15. እ.ኤ.አ በ1933 ከወጣው እና 137 አንቀጾች ከነበሩት የንግድ ማኅበራት ሕግ እና በ1924 ወይም 1925 ይውጣ በውል ከማይታወቀው ብድርን የተመለከተ ሕግ ውጭ ከረቂቅነት ያለፈ ፋይዳ ያለው ይህ ነው የሚባል ሕግ አልነበረም ለማለት ያስደፍራል።

[2] ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድርን በተመለከተ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 132-134፤ ነጋዴ ስለሚነግድበት ስም በአንቀጽ 135-139፤ መያዝ ስላለባቸው የሂሳብ መዛግብት ይዘት እና አያያዝ በአንቀጽ 66-70 እና 73-85 ሥር የተመለከቱት ድንጋጌዎች በወቅቱ የነበረውን የሕግ ክፍተት ለመሙላት የተካተቱ ቅንጭብጫቢ ድንጋጌዎች ይመስላሉ።

[3] Peter Winship (ed. and translator), Background Documents to the Ethiopian Commercial Code of 1960 (Haileselassie I University 1974)፣ ገጽ 12።

ውሳኔዎች ነበሩ። እነዚህንም በንግድ ሕጉ የማርቀቅ ሂደት ታሳቢ ማድረግ የግድ ነበር። በተጨማሪም ፕሮፌሰር ኤስካራ ሥራውን ሲጀምሩ እንዳመለከቱት የእንግሊዝ ሕግ አንዳንድ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚያስቀምጣቸው ድንጋጌዎች የተሻለ ነው ብለው በሚያምኑባቸው ሁኔታዎች ለማካተት ተሞክሯል።[4] በመሆኑም የንግድ ሕጉ የተለያዩ አገሮችን እና የሕግ ሥርዓቶችን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው። በዋናነት ግን የንግድ ሕጋችን የኢትዮጵያ መንግሥት በጠየቀው መሠረት የተጻፈ የሕግ ሥርዓት ልምድ ያካበቱ የምዕራብ አውሮጳ የሕግ ልማድን ("ሲቪል ሎ ትራዲሽን") እና ተሞክሮን በመቀመር የተሰናዳ ነው።

## 2. ሕጉን ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት

ፕሮፌሰር ኤስካራ ለንጉሠ ነገሥቱ የሕግ አርቃቂ ኮሚሽን ባቀረቡበት የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ላይ የሚያዘጋጁት ረቂቅ እጅግ ዘመናዊ መሆን አለበት ብለው እንደማያምኑ ገልጸው ነበር። አንድ ሕግ ሕጉ የሚዘጋጅለትን አገር ተጨባጭ የኢኮኖሚ፣ የንግድ ልማድ፣ ተቋማት እና ባህል ወዘተ ታሳቢ ማድረግ እንዳለበት አርቃቂው እምነታቸውን ገልጸዋል። በተለይም ዘመናዊ ተቋማት እና የተራቀቀ የንግድ አሠራር ያላቸው አገሮችን ሕጎች መሰረት ያደረገ ሆኖም ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማይጣጣም እጅግ ዘመናዊ የንግድ ሕግ ገልብጦ ማምጣት ከባድ ስህተት እንደሆነ አመልክተዋል።[5] በመሆኑም ሕጉ በተጨባጭ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን የንግድ ልማዶች እና አሰራሮችን በጽሁፍ ከማስፈር ያለፈ መሆን እንዳለበት ጠቁመው ሆኖም በጣም የተራቀቀ እና ሥራ ላይ ሊውል የማይችል መሆን እንደሌለበት ፕሮፌሰር ኤስካራ በአጽንዖት ገልጸዋል።[6]

የሚያረቁት የንግድ ሕግ ከሚወጣበት ጊዜ ጀምሮ በሃያ አምስት ዓመት እጅግ ቢበዛ ደግሞ በሃምሳ ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚፈጠሩት ተለዋዋጭ የኢኮኖሚ እና ንግድ እንቅስቃሴዎች ጋር የሚስማማ እና ለውጦቹን ሊያስተናግድ የሚችል መሆን እንዳለበት አርቃቂው አመልክተዋል።[7] በመሆኑም የንግድ ሕጋችን መሠረታዊ የሚባል ማሻሻያ ሳይደረግበት አርቃቂው ካሰቡት የመጨሻው ረጅም ጊዜ (ሃምሳ ዓመት) በላይ ቆይቷል ማለት ነው። ስለዚህ ሕጉን ለመፈተሽና ለማሻሻል በሕጉ አርቃቂዎች ዕይታ እንኳን ጊዜው ረፍዷል።

ሥራ ላይ በዋለባቸው ያለፉት ስድስት ዓስርት ዓመታት በተለይ ደግሞ አገራችን ገበያ-መር ሥርዓት በተከተለችባቸው ሃያ ስምንት ዓመታት የንግድ ሕጋችን በተግባር ሊፈተሽ ችሏል። በመሆኑም ሕጉ ውስጥ ለትርጉም የተጋለጡ፣ ለትግበራ የማይመቹ እና ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማይሄዱ ድንጋጌዎች እንዳሉ ግልጽ ሆኗል። በተጨማሪም በ1952 ዓ.ም ከነበረው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ሕጉ እጅግ ዘመናዊ እንደነበረ ባይካድም ዛሬ አገራችን ከደረሰችበት የንግድ እንቅስቃሴ ደረጃ አንጻር ብዙ ክፍተቶች ያሉበት መሆኑ አያከራክርም።

ከዚህም ባሻገር የአንድ አገር የንግድ ሕግ በተቀረው ዓለም ላይ ያሉ የንግድ ሕጎችን፣ አሰራሮችን እና ለውጦችን ታሳቢ ማድረግ ይኖርበታል። በቴክኖሎጂ እና የመገናኛ ዘዴዎች እጅግ መዘመን የተነሳ ዓለም ወደ አንድ መንደርነት እየተለወጠ ባለበት ሁኔታ የሌላውን ዓለም ሕግ፣ ልምድ እና ተሞክሮ ታሳቢ ያላደረገ ሕግ አገራችንን ዋጋ ያስከፍላታል። የንግድ እና የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት በጣም በፍጥነት እያደገ እና ዓለም አቀፋዊ ባሕሪ እየተላበሰ መጥቷል። በመሆኑም የንግድ ሕጋችን

[4] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 14

[5] ዝኒ ከማሁ ገጽ 1

[6] ዝኒ ከማሁ

[7] ዝኒ ከማሁ

ኢትዮጵያ ውስጥ ሀብታቸውን ለማፍሰስ ከተለያዩ የዓለማችን ጫፎች የሚመጡትን ባለሃብቶች ፍላጎት፣ አሰራር እና ልምድ ታሳቢ ማድረግ አለበት። ስለዚህ የንግድ ሕጉ ላለንበት ጊዜ የሚመጥን መሆኑን መፈተሽ የግድ ይላል።

ከዚህም ባለፈ ሕጋችን ሲቻል ሲቻል በቀጣዮቹ ሃያ አምስት እና ሰላሳ ዓመታት ለሚኖረው የንግድ እንቅስቃሴ ጥርጊያ መንገድ የሚያሰናዳ መሆን አለበት። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ዛሬ መዋዕለ ነዋያቸውን የሚያፈሱ ባለሃብቶች የሥራቸውን ውጤት ለመተንበይ ይቸገራሉ። በመሆኑም ለኢንቨስትመንት አገራችን በሚኖራት ተመራጭነት ላይ ሕጉ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ የንግድ ሕጋችንን መፈተሽ እና አስፈላጊ ማሻሻያዎች ማድረግ ለነገ ይደር የሚባል ጉዳይ አይደለም።

በዚህ ምክንያት የንግድ ሕጉን ለማሻሻል ከደርግ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በመንግሥት እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ጥናቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። በተለይ ባለፉት አምስት ዓመታት ሕጉን የማሻሻል ሥራ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ሙሉ ትኩረት በማግኘቱ ብዙ ጥናቶች ተከናውነዋል። የውይይት መድረኮችም ተዘጋጅተዋል። በጥናቶቹ እና በውይይቶቹ መሰረታዊ ችግሮች ተብለው ከተለዩት ውስጥ የሚከተሉትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡-

1. በንግድ ሕጉ ውስጥ የሚገኙት ስለንግድ ምዝገባ፣ የንግድ ስም፣ የንግድ መደብር መያዣነት እና መሰል ሌሎች ጉዳዮች የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች በተመለከተ በየጊዜው ከወጡት ሕጎች ጋር የሚጣጣሙ እና የተሟላ ተመጋጋቢነት የሌላቸው መሆኑ፤
2. በንግድ ሕጉ ውስጥ ያሉት የሒሳብ አያያዝ ድንጋጌዎች ግልጽ ካለመሆናቸውም በተጨማሪ ከዘመናዊ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት አንጻር አመቺ አለመሆን እንዲሁም ከአምስት ዓመት በፊት ከወጣው ጉዳዩን ከሚመለከት አዋጅ ጋር ሙሉ ተደጋጋፊነት የሌላቸው መሆኑ፤
3. በኩባንያዎች ውስጥ አነስተኛ ድርሻ ይዘው የሚገቡትን ባለሃብቶች ከዘረፋ፣ ካልተገባ ጭቆና ወይም በደል ለመታደግ ያለሙ ድንጋጌዎች በንግድ ሕጉ ውስጥ ከሞላ ጎደል ያልተካተቱ መሆን በዚህም የተነሳ ኢኮኖሚው ያፈራውን አነስተኛ ካፒታል በተሟላ ሁኔታ በተደራጀ መልክ ሥራ ላይ ማዋል አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱ፤
4. በኩባንያዎች ውስጥ አነስተኛ ድርሻ ላላቸው ባለሃብቶች መብት የሚደረገው ጥበቃ መላላት በአገር ውስጥ የተቀጠበውን ካፒታል በተሟላ መልክ ሥራ ላይ ማዋልን ከመገደቡ አልፎ አገሮች ለንግድ ምን ያህል አመቺ እንደሆኑ በሚለኩ በዓለም ባንክ እና መሰል ተቋማት በሚደረግ ዓለም አቀፍ ምዘናዎች ኢትዮጵያ በየዓመቱ በጣም ዝቅተኛ ውጤት እንድታገኝ ማድረጉ፣ በዚህም የተነሳ አገራችን የውጭ ኢንቨስመንት ለመሳብ በምታደርገው ጥረት ላይ ዕንቅፋት መሆኑ፤
5. ባለሃብቶች በንግድ ማኅበራቸው ሥራ አመራር ላይ ሊኖራቸው ስለሚገባው ቁጥጥር የተዘረጋው ሥርዐት ብዙ ክፍተቶች ያሉበት መሆኑ፤
6. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሲፈርስ የሒሳብ ማጣራት ሥራ እንዴት መደረግ እንዳለበት በተለይም ስለ ሒሳብ አጣሪዎች ሹመት፣ ሥልጣን፣ ኃላፊነት፣ የትርፍ እና ኪሳራ አከፋፈል ወዘተ... የንግድ ሕጉ ምንም ድንጋጌ ያላካተተ መሆኑ፤
7. በኩባንያዎች መካከል ዝምድና በሚኖርበት ጊዜ ከእህትማማች ኩባንያዎች ገንዘብ የመጠየቅ መብት ላላቸው ሰዎች እንዲሁም በኩባንያዎቹ ውስጥ አነስተኛ ድርሻ ላላቸው ሰዎች መደረግ ስላለበት ጥበቃ ሕጉ ድንጋጌዎች የሌሉት መሆኑ፤

8. የንግድ ማኅበራትን መዋሃድ፣ መከፋፈል እና የቅርጽ (ዓይነት) ለውጥ ማድረግ የሚመለከቱት የንግድ ሕጉ ክፍሎች እጅግ ሰፊ ክፍተቶች ያሉባቸው መሆኑ፤
9. ሕጉ ከወጣ ስልሳ ዓመታት ሞልቶት እያለ እንኳን ሥራ ላይ ውለው የማያውቁ የተመላላሽ ሒሳብ ውል (አንቀጽ 925 እስከ 937) እና መሰል ሌሎች ድንጋጌዎች ያሉ መሆኑ፤
10. ባለንበት ዘመን በሌላው ዓለም በስፋት ሥራ ላይ የዋሉ በንግድ ሕጋችን ውስጥ ግን ያልተካተቱ የንግድ ማኅበራት አደረጃጀት አማራጮች መኖራቸው፤
11. የንግድ ማኅበራትን አመራር እና ማኅበራቱ ከሦስተኛ ወገን የሚኖራቸውን ግንኙነት ዘመን አፈራሽ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የተሳለጠ እና ግልጽነት የሰፈነበት በማድረግ ረገድ ሕጉ ኋላቀር እና እንቅፋት ፈጣሪ ሆኑ መገኘቱ፤
12. በውጭ አገር የተመሰረቱ የንግድ ድርጅቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ሲከፍቱ ከእነዚህ ድርጅቶች ገንዘብ የመጠየቅ መብት ለሚኖራቸው ሰዎች መደረግ ስላለበት ጥበቃ እና ሊሰጣቸው ስለሚገባ መረጃ የንግድ ሕጉ ምንም ዓይነት ድንጋጌዎች የሌሉት መሆኑ፤፣
13. የተቀማጭ ምስክር ወረቀት (Deposit Ccertificate)፣ የጉምሩክ ሰነድ (Customs Receipts) ወይም የዕቃ መልቀቂያ፣ የማስረከቢያ ትዕዛዞች (Delivery orders) ወዘተ... በብዙ አገሮች ውስጥ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ዓይነት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ይታወቃል። ሆኖም እነዚህንና መሰል ሰነዶችን በመጠቀም የሚሰሩ ስራሥራዎች (transactions) በተመለከተ የንግድ ሕጉ የሚደነግገው ነገር አለመኖሩ፤
14. በንግድ ሕጉ እንዲኖራቸው ከታሰበው ዓላማ ውጭ በስፋት ሥስራ ላይ እየዋሉ የሚገኙ ቼክን እና የመሳሰሉ የክፍያ ሰነዶች የሚመለከተውን ሕግ ይበልጥ ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ፤
15. በሌላው ዓለም መዋዕለ ንዋይን ሥራ ላይ ከማዋል ጋር በተያያዘ ኢንቨስትመንት ባንኪንግ የተሰኘ ራሱን የቻለ የባንክ አገልግሎት ዓይነት በእጅጉ የተለመደ ሆኖ ሳለ የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ስለዚህ የባንክ ሥራ ምንም ዓይነት ድንጋጌዎችን ያካተተ አለመሆኑ፤
16. ከወለድ ነጻ የባንክ ሥራዎች (እስላማዊ ባንኪንግ) የራሱ የሆኑ ጽንሰ ሀሳቦች እና ዝርዝር አሰራሮች ያሉት የባንክ አገልግሎት ሆኖ ሳለ እና በተጨባጭም በዚህ ረገድ ብዙ ያልተሟላ ፍላጎት እና ጅምር አገልግሎት ቢኖርም ይህ ዓይነቱ የባንክ ሥራ በንግድ ሕጉ ከተካተተው የባንክ አገልግሎቶች ሕግ ጋር እንዴት ማስኬድ እንደሚቻል የሚደነግግ ሕግ አለመኖሩ፤
17. ኤሌክትሮኒክ የክፍያ ዘዴዎችን የሚመለከቱ ሥራዎች፣ ኤሌክትሮኒክ ክሬዲት የማስተላለፊያ አሰራር፣ የክፍያ ካርዶች (ATM/debit cards) ሥራዎች፣ የሞባይል ባንኪንግ ሥራዎች፣ የኢንርኔት ባንኪንግ ሥራዎች (transactions) በተጨባጭ ሥራ ላይ መዋል የጀመሩ ሲሆን የተሟላ የሕግ መሠሰረት እና አሠራር ያልተዘረጋላቸው መሆኑ፤
18. በንግድ ሕጋችን በመጽሐፍ አምስት ሥር የሚገኘው የኪሳራ ሕግ ዓላማ፣ ሕጉን በማስፈጸም ረገድ ተሳትፎ ያላቸው አካላት ማንነት፣ ሚና እና ግንኙነት በተመለከተ ቀላል የማይባል ብዥታ መኖሩ፤
19. የንግድ ሕጉ የንግድ ድርጅቶች ባይከስሩም በተለያዩ ምክንያቶች ለጊዜው የገንዘብ እጥረት ሊያጋጥማቸው እንደሚችል እና በድርድር ዋና ዋና ገንዘብ ጠያቂዎች ለጊዜው ፋታ ከሰጡዋቸው ከመክሰር ሊድኑ እንደሚችሉ ታሳቢ ያደረገ ለጥንቃቄ የሚደረግ ዕዳን መልሶ የማዋቅር ሥነ-ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤
20. በንግድ እንቅስቃሴዎች የመቀጠል ተስፋቸው ያልተሟጠጠ ሆኖም የሕግ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ድርጅቶችን ለመታደግ በ1952 የንግድ ሕጋችን "የመጠበቂያ ስምምነት" (schemes of arrangement) በሚል ርዕስ ሥር የተካተቱት ድንጋጌዎች ግልጽነትና ምሉዕነት የሚጎድላቸው ከመሆኑም ባሻገር እምብዛም ውጤት በማያስገኝ አኳኋን የተደገጉ ሆነው መገኘታቸው፤ በተለይም ይህ ዓይነቱ ሥስርዓት የሚከፈትባቸው መሥስፈርቶች፣

ሥስርዓቱ ተግባራዊ የሚደረግበት የጊዜ ገደብ እና ይህን ሥስነ-ሥስርዓት ስኬታማ ለማድረግ ገንዘብ ለሚያቀርቡ አዲስ አበዳሪዎች የሚደረግ የሕግ ጥበቃ እና ሥስርዓቱ እንዲጀመር ስለሚወሰንበት አኳሃን ሕጉ ያልተሟላ ሆኖ መገኘቱ፤

21. ዕዳን መልሶ የማደራጀት ዕቅድ ተቀባይነት ቢያጣ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የነጋዴውን (የንግድ ማህበሩን) ሃብት አንድ በአንድ ከመሸጥ ይልቅ የንግድ ድርጅቱን በሥራ እንቅስቃሴ ላይ እንዳለ ባለበት ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ አማራጭን የንግድ ሕጋችን አለማካተቱ፤ እና
22. የኪሳራ ሥነ-ሥርዓት የሚከፈትባቸው መስፈርቶች፣ የሥነ-ሥርዓቱ መከፈት የሚኖረው ውጤት፣ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸምባቸው ሰዎች/አካላት፣ በኪሳራው ሥነ-ሥርዓት መፈጸም የተገኘ ገንዘብ ክፍፍል እና የከሰረው ሰው ከዕዳ ነጻ የሚሆንበት ሁኔታዎች በተመለከተ የንግድ ሕጉ የተሟሉ እና ግልጽ ድንጋጌዎች ያካተተ ሆኖ አለመገኘቱ ተጠቃሽ ናቸው።

## 3. የንግድ ሕግ የማውጣት ሥልጣን የፌዴራል መንግሥት ስለመሆኑ

የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት በምዕራፍ አምስት እና ስድሰት ሥር የሀገረ መንግስቱን አወቃቅር በፌዴራል መንግሥትና እና ክልላዊ መስተዳደሮች መካከል ስለሚኖረው የሥልጣን ክፍፍል ይደነግጋል። የፌዴራል መንግስቱን ሥልጣን እና ኃላፊነት የሚዘረዝረው አንቀጽ 51 አገር አቀፍ ፋይዳ ባላቸው የንግድ እና ኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ሥልጣን ያለው የፌዴራል መንግስት መሆኑን ያመላክታል። በተለይ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 4 የንግድ ሕግ መድብል (ኮድ) ማውጣት የፌዴራል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥልጣን መሆኑን ቃል በቃል በማያሻማ ሁኔታ አስቀምጧል።

ስለዚህ በቀረበው የንግድ ሕግ ረቂቅ ላይ ተወያይተው የማጽደቅም ሆነ ያለማጽደቅ የሚንስትሮች ምክር ቤት ብሎም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መሆኑ በሕገ መንግስቱ በግልጽ ተደንግጓል።

## 4. ሕጉ የተረቀቀበት ሂደት

የንግድ ሕጉን ለመፈተሽና ለማሻሻል ደርግ በመንግሥት ስልጣን ላይ ከነበረበት ጊዜ አንስቶ በተለያዩ ጊዜያት ጥረት ሲደረግ መቆየቱ ከላይ ተወስቷል። ለዚህም በምሳሌነት በቀድሞ የፍትሕ ሚኒስቴር እንዲሁም የፍትሕ እና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት በተለያዩ ጊዜያት ያዘጋጁትን ረቂቆች መጥቀስ ይቻላል። አልፎ ተርፎም ከአሥራ ሁለት ዓመት በፊት ተዘጋጅቶ የነበረው ሙሉ ረቂቅ የንግድ ሕግ ላይ የንግድ ማኅበረሰቡ በተደራጀ መልክ አስተያየት እንዲሰጥበት መጠየቁ ይታወሳል። በዚህ መነሻነት የአዲስ አበባ የንግድ ምክር ቤት አሥራ አራት ከፍተኛ ኤክስፐርቶች ያሉበት ቡድን አዋቅሮ ረቂቅ ሕጉን በጥልቀት አስጠንቷል። በጥናቱ መነሻነትም የንግድ ማሕበረሰቡን አቋም የሚያንጸባርቅ 130 ገጽ ያለው ሪፖርት እ.ኤ.አ በ2009 ማቅረቡ ይታወቃል። ከዚህም በኋላ የፍትህ ሚኒስቴር ረቂቁን ከንግድ ማሕበረሰቡ እና ከሌሎች ባለድሻዎች በተገኘው አስተያየት መሰረት ያዳበረ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች የንግድ ሕግ ክለሳው ከዳር ሳይደርስ ቀርቷል።

በመሆኑም የፍትሕ ሚኒስቴር (የአሁኑ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ) በ2006 ዓ.ም ሥራውን በአዲስ መልክ ለማሰራት ተንቀሰቅሶ ወቅቱ ከነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ደብዳቤ ተጽፎ ከጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት፣ ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን፣ ከኢትዮጵያ መድህን ድርጅት፣ ከብሄራዊ ባንክ፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ከአዲስ አበባ ፍትህ ቢሮ፣ ከሕግና ፍትህ ምርምርና ሥልጠና ኢንስቲትዩትና ከፍትህ ሚኒስቴር የተውጣጡ ባለሙያዎችን የያዘ

አምስት ቡድን በማቋቋም ኮሚቴው በአዲስ መልክ በአምስቱም መፅሀፎች ላይ ለ6 ተከታታይ ወራት ከሌላ ሥራ ውጪ ሆነው በቢሾፍቱ ከተማ ጥናቱን እንዲያከናውኑ አድርጓል። ጥናቱ ከተሰራ በኋላ በጥናቱ ላይ በተከታታይ ከሚመለከታቸው አካላትና ከጥናት ቡድኑ አባላት ጋር በዝርዝር ውይይት የተደረገ ሲሆን በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ አቅጣጫ ተሰጥቶ ወደ ማርቀቅ ተገብቷል። ረቂቁ ሲሰራ ጥናቱን፣ ከዚህ በፊት የተሰሩ ረቂቆችንና ሌሎች ጥናቶችን መነሻ በማድረግ ለማርቀቅ ጥረት የተደረገ ሲሆን፣ ባለሙያዎቹም በተመለከተ ጥናቱን የሰሩትን እንደመነሻ በመያዝ ተጨማሪ ባለሙያዎችም እንዲካተቱ በማድረግ ሥራውን ለመሥራት ተችሏል።
ረቂቁ ከተጠናቀቀ በኋላ ብሄራዊ ባንክ ሥራውን እየመራው በርካታ ውይይቶችን ከመንግሥትና ከግል ባንኮችና ኢንሹራንስ ድርጅቶች ጋር በማድረግ ግብዓት ለማሰባሰብ ጥረት የተደረገ ሲሆን፣ በጉዳዩ ላይ ተደጋጋሚ ውይይት በማድረግ ግብዓት ማሰባሰብ አስፈላጊ በመሆኑ ከብሄራዊ ባንክ፣ ከንግድ ባንክ፣ ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት፣ ከልማት ባንክ፣ ከግል ንግድ ባንኮች፣ ከግል ኢንሹራንስ ድርጅቶች፣ ከታዋቂ ነጋዴዎች፣ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች፣ ከገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ከሕግ ጥናትና ምርምርና ፍትህ አካላት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት፣ ከሕግ ባለሞያ ሴቶች ማኅበር፣ ከጠበቆች ማኅበር፣ ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር፣ ከንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፣ ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት፣ ከህዝብ ተወካዩች ም/ቤት የሕግ፣ ፍትህና አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ፣ ከዘጠኙም ክልል ፍትህ ቢሮዎች፣ከዘጠኙም ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች፤ ከሕግ ትምህርት ቤቶች፣ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ አየር መንገድና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር ሰፊ ውይይት ተደርጎ ግብዓት ማሰባሰብ ሥራ ተሰርቶ ረቂቁን ለማጠናቀቅ ተችሏል።

በወቅቱ ረቂቁን ለማጠናቀቅ የተቻለ ቢሆንም ከ2010 ጀምሮ በመጣው ለውጥ ቅኝት ሪፎርም ማካሄድ በማስፈለጉ እና ከዚህ በፊት የተሰሩ ረቂቆችንም ጭምር እንደገና መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ተነሳሽነት አገር አቀፍ የፍትህ እና የሕግ ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ መመስረቱ ይታወሳል። የንግድ ሕጉ ረቂቅ ከላይ እንደተመለከተው በረጅም ሒደት እና በሰፊ የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ የተዘጋጀ ቢሆንም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የንግድ ሕግ ጉዳይ ልዩ ጥንቃቄ እንደሚሻ በመገንዘብ ለመጨረሻ ጊዜ በአማካሪ ጉባኤው ባለሞያዎች እንዲታይ ወስኗል። በመሆኑም ከሐምሌ ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ ረቂቁ በፍትህ እና የሕግ ጉዳዮች ጉባኤ እንዲታይና ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊ ለውጥ እንዲደረግበት ተደርጓዋል።

ጉዳዩ የተመራለት አማካሪ ጉባኤም የንግድ ሕጉ በጣም ቴክኒካዊ እና ውስብስብ መሆኑን በመገንዘብ በዘርፉ እጅግ የተሻለ ልምድ ያካበቱ 24 (ሃያ አራት) አባላት ያሉበት የሥራ ቡድን አዋቅሮ፤ የሥራ ቡድኑ ረቂቁን በማጥናት አስፈላጊ ያላቸውን የለውጥ ሀሳቦች እንዲያቀርብ አድርጓዋል። የአማካሪ ጉባኤው የሥራ ቡድን እና በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በተቀናጀ ሁኔታ ረቂቅ ሕጉን በድጋሚ በመፈተሽ፣ ረቂቁ እንዲከለስ ተደርጓዋል።

በዚህ ሂደት ውስጥ ከንግድ ሕጉ ውስጥ የኪሳራ ሕግ (bankruptcy law) ብዙም በተግባር ያልተፈተሸ ከመሆኑም በላይ በቂ የባለሞያ አቅም በአገር ውስጥ ስለሌለ የውጭ ኤክስፐርቶች ሙያዊ እገዛ እንዲያገኙ ተደርጓል። በዚህም መሰረት ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር ተቀራራቢነት ካለው ከፈረንሳይ አገር ስመጥር በሆነው በፓሪስ ሶርቦን ዩኒቨርሲቲ የኪሳራ ሕግ መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር ራይናርድ ዳማን ረቂቁን ከመገምገማቸውም በላይ አዲስ አበባ በመምጣት ከሥራ ቡድኑ ጋር በቅርበት ሰርተዋል። ከዓለም ባንክም የኪሳራ ሕግ ከፍተኛ ባለሙያዎች በሥራው ተሳትፈዋል። በአጠቃላይ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እና በሕግና ፍትህ አማካሪ ም/ቤት ሥር የተቋቋመው የሥራ ቡድን ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን ለ16 ወራት በመሥራት ቀደም ሲል የተዘጋጀውን ረቂቅ ድጋሚ በማየትና በማሻሻል ይህን ረቂቅ አዘጋጅተዋል።

## 5. እንደ ማጣቀሻ የተወሰዱ ሕጎችና ሰነዶች

ከላይ እንደተመለከተው የንግድ ሕጋችን የተረቀቀው የሲቪል የሕግ ሥርዓት የሚከተሉት የምዕራብ አውሮጳ በዋናነት ደግሞ የፈረንሳይን ሕግ መሰረት በማድረግ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ከሌሎች አገሮች ሕጎች እና ልምድ ለኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተስማሚ ናቸው ተብለው የታሰቡ ሃሳቦችም ተካተዋል፡፡ የዚህ ረቂቅ ሕግ ዝግጅት በተመሳሳይ ዕሳቤ ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ በተቻለ መጠን የሕጋችን እናት ሕጎች ናቸው በተባሉት የምዕራብ አውሮጳ ሕጎች ላይ ትኩረት ተደርጓል፤ በተጨማሪም ከኢትዮጵያ ጋር በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ ያሉ አገሮች ተሞክሮ እና ሕጎች ታይተዋል፡፡ በተለይ ረቂቁ በሚሸፍናቸው ጉዳዮች ላይ ሕግ ማውጣት ለሚፈልጉ አገሮች ናሙና (ሞዴል) እንዲሆኑ በተለያዩ አህጉራዊ እና ክፍለ-አህጉራዊ ድርጅቶች የተዘጋጁ ሕጎች በስፋት ግምት ውስጥ ገብተዋል፡፡ ለዚህ ጉዳይ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ረቂቅ ሕጉ በተቻለ መጠን አዳዲስ አስተሳሰቦችን እና አሰራሮችን ታሳቢ ያደረገ እና በተቻለ መጠን ለረጅም ጊዜ ተወዳዳሪ እና የሚያሰራ ሆኖ እንዲቆይ በማሰብ ማጣቀሻ ተደርገው የተወሰዱ ሕጎች እና ናሙናዎች በተቻለ መጠን በቅርብ ዓመታት የተዘጋጁ እንዲሆኑ ጥረት ተደጓል፡፡

ከላይ በተገለጹት መመዘኛዎች መሰረት ተመርጠው በስፋት ለማጣቀሻነት ሥራ ላይ የዋሉት ዋና ዋናዎቹ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፡-

1) እ.ኤ.አ 20 ማርች 2006 ድረስ የተደረጉ ለውጦችን ያካተተ የፈረንሳይ የንግድ ሕግ፤
2) እ.ኤ.አ 9 ዲሰምበር 2010 ድረስ የተደረጉ ለውጦችን ያካተተው የጀርመን የኩባንያ ሕግ፤
3) እ.ኤ.አ በ2017 በተለያዩ የአውሮጳ አገሮች ባለሙያዎች በጋራ ተሰናድቶ የወጣው የአውሮጳ ሞዴል የኩባንያ ሕግ (European Model Company Act)፤
4) የምዕራብ አፍሪካ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ አገሮች ሕግ ወጥ ለማድረግ እ.ኤ.አ በጥር 2014 የወጣው UNIFORM ACT ON COMMERCIAL COMPANIES AND THE ECONOMIC INTEREST GROUP፤
5) የዓለም ባንክ ለንግድ ሥራ አገሮች ያላቸውን አመቺነት ለማወዳደር ካወጣቸው መመዘኛዎች አነስተኛ ድርሻ ላላቸው ባለአክሲዮኖች የሚደረግ ጥበቃን የተመለከተው መጠይቅና ማብራሪያ፤
6) እ.ኤ.አ በ1 ጁላይ 2012 ሥራ ላይ የዋለው የቱርክ የንግድ ሕግ (አዋጅ ቁ. 6102
7) እ.ኤ.አ 2009 ድረስ የተደረጉ ለውጦችን ያካተተ የደቡብ ኮሪያ የንግድ ሕግ፤
8) እ.ኤ.አ በ29 ኦገስት 2013 የወጣው የሕንድ የኩባንያ ሕግ (ሕግ ቁ. 18/2013)፤
9) እ.ኤ.አ በ2006 የወጣው የእንግሊዝ የኩባንያ ሕግ፤
10) እ.ኤ.አ በ27 ኦክቶበር 2005 የተሻሻለው የቻይና የኩባንያ ሕግ፤
11) የቅድመ ጥንቃቄን መልሶ ማዋቀር ሥነ ሥርዓት በተመለከተ የተሻለ ሥርዓት ዘርግታለች ተብሎ ከሚነገርላት ፈረንሳይ እንዲሁም ይህንኑ ተገንዝቦ በቅርቡ የአውሮፓ ህብረት ካወጣው መመርያ ጠቃሚ ድንጋጌዎችንና ሥነ ሥርዓቶች፤

12) የመልሶ ማደራጀትና የኪሳራ ሥነ ሥርዓትን በተመለከተ በዚህ ረገድ የደረጀ ልምድ ካላት አሜሪካ ጠቃሚ የሚባሉ ድንጋጌዎች፤

13) በአሥራ ሰባት የአፍሪካ አገራት ወጥና ተስማሚ የሕግ ሥርዓትን ለመዘርጋት በተቋቋመው ማኅበር OHADA (organization pour l'harmonisation en Afrique du droit des affairs) ጥላ ሥር ከወጡት ተስማሚ ህጎች መካከል UNIFORM ACT FOR BANKRUPTCY PROCEEDINGS ከሚባለው ሕግ ለኢትዮጵያ ተስማሚ ናቸው ተብለው የተገመቱ ድንጋጌዎች፤

14) የተባበሩት መንግሥታት የዓለም አቀፍ ንግድ ኮሚሽን (UNITED NATIONS COMMISSION ON INTERNATIONAL TRADE LAW) ያሳተመው UNCITRAL LEGISLATIVE GUIDE ON INSOLVENCY LAW ፤

15) የዓለም ባንክ ኪሳራን በተመለከተ ያወጣቸው መርሆዎች THE WORLD BANK'S PRINCIPLES FOR EFFECTIVE INSOLVENCY AND CREDITOR/DEBTOR REGIMES፤

16) የኢትዮጵያ የ1952ቱ የንግድ ሕግ መፅሐፍ 5 (በተለምዶ የኪሳራ ሕግ ተብሎ የሚጠራው) በተግባር ብዙም ባይፈተሽም በሥራ ላይ በዋለባቸው ጥቂት መዝገቦች የኪሳራ ሂደቶች ላይ የተሰጡ ውሳኔዎችና ትዕዛዞች እንዲሁም በየደረጃው በፍ/ቤቶችና በኃላፊዎቹ የተወሰዱ እርምጃዎችና ውሳኔዎች በዚህ ሂደት የታዩ ዕክሎችና ተግዳሮቶች፤

17) በዓለም ባንክ የንግድ ሥራ አመቺነት ምዘና (WORLD BANK DOING BUSINESS INDEX) አንዱ መስፈርት የዕዳን መክፈል ማቋረጥ ሥነ ሥርዓት ሲሆን (RESOLVING INSOLVENCY) የዓለም ባንክ እንደ መልካም ማሻሻያዎች የሚላቸውን መስፈርቶች።

# 6. የረቂቅ ሕጉ ዋናዋና ይዘቶች

## 6.1 የረቂቅ ሕጉ ከ1952ቱ የንግድ ሕግ ጋር ሲነጻጸር

በ1952 ከወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንጻር ረቂቁን በንጽጽር በመመልከት የረቂቅ ሕጉን ይዘት በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል። ሆኖም አንቀጽ በአንቀጽ ረቂቁን እና የ1952ቱን አዋጅ ማነጻጸር እጅግ ሰፊ ጉዳይ በመሆኑ እና ለዚህ ሰነድ ዓላማ አስፈላጊ ስላልሆነ፤ አሁን ሥራ ላይ ያለው ሕግ የሸፈናቸውን አንኳር አንኳር ርዕሰ ጉዳዮች በማንሳት ረቂቁ ሕግ በእነዚህ ዙሪያ ምን ለውጥ ያደርጋል የሚለውን ለማስረዳት ማሳያ የሚሆኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ያተኮረ ማብራሪያ እንደሚከተለው ቀርቧል።

### ሀ) አሁን በሥራ ላይ ያለው የንግድ ሕግ ለሁለት ተከፍሎ የንግድ ሕግና የፋይናንስ አገልግሎቶች መድብል (ኮድ) በሚል ሁለት ራሳቸውን የቻሉ መድብሎች / እንዲወጡ መደረጉን በተመለከተ የቀረበ ሐሳብ

ሥራ ላይ ያለው የንግድ ሕጋችን ሁለት የተለያዩ ጉዳዮችን እንደያዘ መገንዘብ ይቻላል። አንደኛው የንግድ ሕጉ ይዘት በአንድ የንግድ ድርጅት ሕይወት ላይ ያተኮረ (enterprise centric) ነው። ጠቅለል አድርገን ስንመለከት የንግድ ሕጉ መጽሐፍ አንድ እና መጽሐፍን ሁለት ድንጋጌዎች የአንድን የንግድ ድርጅት አመሰራረት (ውልደት)፣ ድርጅቱ በሥራ ላይ ባለበት ጊዜ የሚነሱ የአመራር ጉዳዮች፣ የአባላት መብት እና ግዴታ እንዲሁም ከድርጅቱ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ላላቸው ሰዎች የሚደረግ የሕግ ጥበቃን ማዕከል ያደረጉ ናቸው። ከእነዚህ ጋር አብሮ የሚሄደው የንግድ ሕጉ መጽሐፍ አምስት ደግሞ አንድ የንግድ ድርጅት ችግር ላይ የወደቀ እንደሆነ ድርጅቱን ለማትረፍ፤ ካልተቻለም የተገኘውን ያክል የድርጅቱን ሃብት ከብክነት

በማዳን ለገንዘብ ጠያቂዎች በፍትሃዊ መንገድ ስለማከፋፈል ይደነግጋል። በአጭሩ እነዚህ ሦስት መጻሕፍት በአንድ የንግድ ድርጅት ልደት፣ ሕይወት እና ሞት ዙሪያ የሚሽከረከሩ ናቸው።

በአንጻሩ የንግድ ሕጋችን መጽሐፍ ሦስት እና አራት የተወሰኑ የሥራ መስኮችን በተመለከተ ስለሚደረጉ ግንኙነቶች/ውሎች (transactions) የሚደነግጉ ናቸው። የመድን አገልግሎት፣ የባንክ ሥራዎች እና የክፍያ አፈጻጸም ዘዴዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ከእነዚህ ሁለት መጻሕፍት ድንጋጌዎች ወደ ሰማንያ በመቶ ይይዛሉ። በተለይ ስለክፍያ መፈጸሚያ መንገዶች እና ሌሎች የባንክ ሥራዎች የሚደነግገው መጽሐፍ አራት 252 አንቀጾች ያሉት እና ሙሉ በሙሉ የፋይናንስ አገልግሎትን የሚመለከት ነው። የሐዋላ ወረቀት፣ የተስፋ ወረቀት፣ ቼክ እና የመሳሰሉት የንግድ ወረቀቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ከመያዙ በተጨማሪ ባንኮች ለደንበኞቻቸው የሚሰጧቸውን ገንዘብ በአደራ ማስቀመጥ፣ ሰነዶችን በአደራ ማስቀመጥ፣ የካዝና ኪራይ፣ ተመላላሽ ሒሳብ፣ ቅናሽ፣ በሰነድ የሚሰጡ ብድሮች እና መሰል የባንክ ሥራዎችን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ይዟል።
መጽሐፍ ሦስት በዋናነት ስለ መድን አገልግሎት ውል እና የሚፈጥራቸውን ግዴታዎች ይደነግጋል። ቀሪዎቹ ድንጋጌዎች ደግሞ በየብስ እና አየር ስለሚደረግ የማጓጓዣ ውል ይደነግጋሉ። በባህር ስለሚደረግ የማጓጓዣ ውል ግን ራሱን የቻለ ኮድ (maritime code) ለብቻው አለ። ስለውርርዶች እና የኪሳራ ጨዋታ የሚደነግጉ ሁለት አንቀጾችም ተካተውበታል።

በአጠቃላይ እነዚህ ሁለት መጻሕፍት ወጥነት (thematic unity) በሌላቸው አራት ዓይነት የሥራ መስኮች ስለሚደረጉ ግንኙነቶች (trasactions) ይደነግጋሉ። ከመድን እና የባንክ ሥራዎች (የፋይናንስ አገልግሎቶች) ውጭ ያሉት ደግሞ ምሉዕነት ያላቸው አይደሉም። ከሌሎች እጅግ ብዙ የሥራ መስኮች በተለየ ሁኔታ በንግድ ሕግ ውስጥ የሚገቡበት አሳማኝ ምክንያት መኖሩም አነጋጋሪ ሆኖ በመገኘቱ ብዙ ውይይት ተደርጎበታል። በተለይ የመድን እና የባንክ ሥራዎች ሕግ የፋይናንስ አገልግሎቶች መድብል (ኮድ) ተብሎ ቢወጣ የተሻለ ይሆናል የሚል ጥያቄም በተደጋጋሚ ተነስቷል። በተደረጉት ውይይትና ተደጋጋሚ ክርክሮች የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ከመግባባት ተደርሷል።

**ለ) <u>መጽሐፍ ሶስት (ስለ ማጓጓዝ ሥራና ኢንሹራንስ)፣ መጽሐፍ አራት (ስለባንክ ሥራዎችና የሚተላለፍ ገንዘብ ሰነዶች) ከመጽሐፍ አንድ፣ ሁለት እና አምስት ጋር ጽንሰ ሐሳባዊ ቁርኝት የሌላቸው ስለመሆኑ</u>**

የባንክ እና መድን አገልግሎት ግንኙነቶችን (transactions) በተመለከተ የሚደነግጉት መጽሐፍ ሦስት እና አራት በአንድ የንግድ ድርጅት ሕይወት ላይ ያተኮሩ (enterprise centric) ድንጋጌዎችን ከያዙት ከመጽሐፍ አንድ፣ ሁለት እና አምስት ጋር ጽነሰ-ሐሳባዊ ቁርኝት እንደሌላቸው ስምምነት ተደርሶበታል። ለምሳሌ የንግድ ሕጉ በእነዚህ መጻሕፍት ድንጋጌዎች መካከል ግንኙነት እንዳለ የሚጠቁም አንድም ማጣቀሻ (cross reference) የለውም። በመሆኑም መጽሐፍ ሶስትና አራት ከመጽሐፍ አንድ፣ ሁለትና አምስት ተነጥሎ የፋይናንስ አገልግሎቶችን የተመለከተ ራሱን የቻለ ኮድ ቢወጣ የሚፈጥረው ጽንሰ-ሐሳባዊም ሆነ የአደረጃጀት (organizational) ችግር ወይም መፋለስ የለም።

**ሐ) <u>የሌሎች አገሮች ልምድ በንግድ ሕግ ውስጥ የግድ እንደማይካተቱ ስለማሳየቱ</u>**

በሌሎች አገሮች ልምድ የባንክ እና የመድን ሥራዎች በንግድ ሕግ ይካተቱ እንደሆነ ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት ተደርጓል። በተለይ ሕጎች በኮድ መልክ የሚወጡባቸው እና ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር ይበልጥ ቀረቤታ ያላቸው የፈረንሳይ፣ የጀርመን፣ የጣሊያን እና ስዊዘርላንድ ሕጎች ተመርምረዋል።

በፈረንሳይ የንግድ ሕግ ውስጥ የባንክ እና የመድን ሥራዎች አልተካተቱም። በፈረንሳይ እነዚህ ሁለት ሥራዎች ራሱን በቻለ ኮዶ ወጥተው፤ ከንግድ ሕጉ በተጨማሪ ሞኒተሪ እና የፋይናንስ አገልግሎቶች (monetary and financial services) ኮድ የተሰኘ ኮድ አለ። ይህ ኮድ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በተመለከተ የውል ግንኙነት (transactional) እና የቁጥጥር (regulatory) ድንጋጌዎችን ያካተተ ነው።

በጣልያን የኩባንያ ሕግ እ.ኤ.አ በ1942 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ መጽሐፍ አምስት ውስጥ ተካቶ ይገኛል። በእርግጥ ይህ ሕግ በተለያዩ ጊዜዎች በወጡ ሕጎች ተሻሽሏል። ለምሳሌ በአክሲዮን ገበያ የተመዘገቡ ኩባንያዎች የሥራ አመራርን በተመለከተ ከፍትሐ ብሔር ሕጉ በተጨማሪ እ.ኤ.አ በ1998 የወጣው Financial Intermediaries Decree No. 58/1998 ተፈጻሚ ነው። የኪሳራ ሕግ ደግሞ ለብቻው ይገኛል። እ.ኤ.አ ከ1942 እስከ 2015 ሥራ ላይ የነበረው የኢጣሊያ የኪሳራ ሕግ Decree No. 267/1942 በመባል የሚታወቀው ሲሆን አሁን ደግሞ Decree No. 83/2015 ተብሎ ለብቻው ወጥቶ ሥራ ላይ ይገኛል።

በተመሳሳይ በሲዊዘርላንድ የኩባንያ ሕግ የሚገኘው ከውል ሕጎች ጋር በፍትሐ ብሔር ሕግ ውስጥ ነው። የኩባንያ ሕጋቸው በፍትሐ ብሔር ሕጉ ርዕስ 26 (ከአንቀጽ 620 እስከ 763) ሥር ይገኛል። ሌሎች የኮዱ ድንጋጌዎችም በተወሰኑ ርዕሰ ጉዳዮች ኩባንያዎች ላይ ተፈጻሚነት አላቸው። ለምሳሌ ርዕስ 31 የኩባንያ ስሞችን በተመለከተ፣ ርዕስ 32 (አንቀጽ 957 እስከ 964) ደግሞ ስለሒሳብ አያያዝ ኩባንያዎች ላይ ተፈጻሚ ናቸው። በጀርመንም የኩባንያ ሕግ ለብቻው ወጥቶ እናገኛለን። የአንግሎ-ሳክሰን የሕግ ልምድ (tradition) የሚከተሉ አገሮች ደግሞ ጭራሽ ኮድ የላቸውም።

**መ) <u>የንግድ ሕጋችን ይዘት ሕጉ በወጣበት ዘመን የነበረው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ነጸብራቅ ሊሆን ስለመቻሉ</u>**

ከላይ እንዳየነው የንግድ ሕጋችን ይዘት እናት ሕጎች ሊባሉ ከሚችሉት የምዕራብ አውሮጳ በተለይ የፈረንሳይ ሕግ መለየቱ ለምን ይሆን? በተለይ የፈረንሳይ የንግድ ሕግ ለምን የባንክ እና የመድን ሥራዎችን አላካተተም? እነዚህን በተመለከተ ፈረንሳይ ለምን የተለየ ኮድ ኖራት የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተው ወይይት ተደርጎባቸዋል።

ከላይ ማየት እንደተቻለው ሁሉም አገሮች የተለያየ መንገድ ተከትለዋል። ይህ የሚያሳየው ምናልባት ሕጎቹ በወጡበት ወቅት በየአገራቱ የነበረውን ተጨባጭ ሁኔታ ነው። በተለይ የንግድ ሕጋችን በወጣበት ዘመን ኢትዮጵያ ይህ ነው የሚባል የተጻፈ ኢኮኖሚ ነክ ሕግ ስላልነበራት የንግድ ሕግ ያረቀቁት ባለሙያዎች በተቻለ መጠን የነበረውን ሰፊ ክፍተት ለመድፈን የጣሩ ይመስላል። ለንግድ ሥራ ስኬት ወሳኝ ድጋፍ የሚሰጡ የፋይናንስ አገልግሎት ሕጎች በሌላት አገር የንግድ ድርጅቶችን ማዕከል ያደረገ (entherprise centric) የንግድ ሕግ ብቻ ቢወጣ የንግድ ሕጉ የተፈለገው ሚና አይኖረውም ብለው ያሰቡ ይመስላል። በመሆኑም የባንክ እና የመድን ጉዳዮች የግድ በንግድ ሕግ የሚካተቱበት ሳይንሳዊም ሆነ ከኮዱ ውስጣዊ የአወቃቀር የመነጨ አስፈላጊነት ባይኖርም እነዚህን ጉዳዮች በሕጉ እንዲካተቱ አድርገዋል። ይህ በወቅቱ የነበረውን ሰፊ የሕግ ክፍተት ለመድፈን የተወሰደ ጥሩ ውሳኔ ቢሆንም ከዚያ ያለፈ ፋይዳ ግን ሊሰጠው አይገባም። በተለይ የፋይናንስ አገልግሎቶችን የተመለከተ ሕግ የግድ በንግድ ሕግ እንዲካተት የሚያስገድድ ሳይንሳዊ ወይም የሥነ አመክንዮ ቁርኝት እንደሌለ ከመግባባት ላይ ተደርሷል።

እንዲሁም የባንክ እና የመድን ሥራዎች ሕግ ለብቻው የፋይናንስ አገልግሎቶች ኮድ ተብሎ ቢወጣ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ይታመናል።

1. **<u>የፋይናንስ አገልግሎቶች ሕግ ከተቀረው ዓለም መራመድ እንዲችል የሚኖረው አመችነት</u>**

ከሌሎች የንግድ ሕግ ጉዳዮች ጋር ሲነጻጸር የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ ከተቀረው ዓለም ጋር የተቆራኘ ነው። ባንኮቻችን ከውጭ አገር ባንኮች ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ተባብረው እየሰሩ ይገኛሉ። ለምሳሌ በዓለም አቀፍ ንግድ እና በተያያዥ የክፍያ አፈጻጸም፣ ለተለያዩ ፕሮክቶች አፈጻጸም የዋስትና ሰነዶች በመስጠት፣ ፕሮጀክቶችን በጋራ ፋይናንስ በማድረግ ወዘተ ባንኮቻችን ከውጭ ባንኮች ጋር በቅንጅት ሲሰሩ እናያለን። ወደፊት የፋይናንስ ዘርፉ ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት የሚሆንበትም ዕድል ሊኖር ይችላል። ይህ ከሆነ የውጭ ባንኮች የተለያዩ ኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ የማይታወቁ አገልግሎቶች ይዘው መምጣታቸው አይቀርም። በተጨማሪም ወደፊት በሌላው ዓለም የሚጀመሩ አዳዲስ የፋይናንስ አገልግሎቶች በቶሎ ወደአገራችን ይገባሉ ማለት ነው። በመሆኑም ሕጋችን እነዚህን አገልግሎቶች በተሟላ አኳኋን የሚገዛ ለመሆን ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ማስተናገድ መቻል አለበት። የፋይናንስ አገልግሎቶች ሕግ ከንግድ ሕጉ ውጭ ሆኖ ለብቻው በኮድ መልክ መውጣቱ አስፈላጊ ለውጦችን በጊዜው ለማድረግ ይረዳል።

2. **<u>የፋይናንስ አገልግሎቶች ሕግ ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር አብሮ እንዲራመድ የሚኖረው ጠቀሜታ</u>**

የፋይናንስ አገልግሎቶች አሰጣጥ ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር የሚለዋወጥ ነው። ለምሳሌ የክፍያ አፈጻጸም ዘዴዎችን መጥቀስ ይቻላል። በመሆኑም ሕጉ ከእነዚህ ተለዋዋጭ ዘዴዎች ጋር በፍጥነት እየተለወጠ በሂደቱ የሚሳተፉተን ሰዎች መብቶች ለመጠበቅ የሚችል መሆን አለበት። ራሱን የቻለ የፋይናንስ አገልግሎቶች ኮድ መኖሩ ሕጉን ለመለወጥና ለማሻሻል የበለጠ ቀላል ያደርገዋል።

3. **<u>በፋይናንስ አገልግሎቶች ሕግ በቂ ባለሙያ በአገር ውስጥ አለመገኘቱ</u>**

የንግድ ሥራን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዘርፉ እያደገ የሚሄድ ቢሆንም በዚህ ዘርፍ በሚፈለገው ደረጃ ብቃት ያለው ባለሙያ በአገር ውስጥ ማግኘት ፈታኝ ነው። አዳዲስ ባንክ አሰራር ሥርዓቶች (ለምሳሌ የወለድ ነጻ አገልግሎት፣ ሞባይል ባንኪንግ፣ ኤሌክትሮኒክስ ክፍያ አፈጻጸም፣ ኢንቨስትመንት ባንኪንግ…) እየተስፋፉ ሲሆን እነዚህን የባንክ አገልግሎቶች፣ አገልግሎቶቹን ለመስጠት ሥራ ላይ የሚውለውን ቴክኖሎጂ እና የሥራ ሂደት በአግባቡ ተረድቶ የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት የሚችል የባለሙያ አቅም ያስፈልጋል። የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ትርጉም ባለው መልክ ለመለወጥ ደግሞ በዚህ ዘርፍ እመርታ ማሳየት እጅግ ወሳኝ ነው። በመሆኑም አስፈላጊ ባለሞያዎችን ከውጭ በማስመጣት ኢትዮጵያዊያን ባለሞያዎች እና ብሔራዊ ባንክን ጨምሮ ባለድርሻ አካላትን አሳትፎ ሰፊ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። ስለዚህ የፋይናንስ አገልግሎቶች ሕግን ጊዜ ወስዶ መሥራት አስፈላጊ ይሆናል። ስለሆነም የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የፋይናንስ አገልግሎቶች ኮድ ሰፊ ጥናት እና እንዳስፈላጊነቱ የውጭ ባለሙያዎች እገዛ ተፈልጎ እንዲረቀቅ ዝግጅት ጀምሯል። ሥራው ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል።

## 6.2 ስለረቂቅ ንግድ ሕጉ አደረጃጀት

አሁን ባለው ሁኔታ የንግድ እና ንግድ ነክ ሕጎች በንግድ ሕጉ፣ ከንግድ ሕጉ በኋላ በወጡ የተለያዩ አዋጆች እና ደንቦች እንዲሁም በፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ በተበታተነ መልኩ ተደንግገው ይገኛሉ። ንግድና ከንግድ ጋር የተገናኙ ግንኙነቶችን የሚገዛ ሕግ በተለያየ መልኩ ተበታትኖ በሚገኝበት ጊዜ በኅብረተሰቡ ዘንድ ከሚፈጥረው የመገንዘብና የመረዳት ችግር በተጨማሪ ለአስፈጻሚ አካላትም ለመረዳትና ለማስፈጸም ችግር ይገጥማል። በተለይም የንግድ ሕግ የተለዩ ባህሪያት (ፍጥነት የሚፈልግ መሆኑ፣ የባለገንዘቡን መብት የመጠበቅና የመከላከል፣ የንግድ ሕግ ዘርፍ በባሕሪውም ሆነ በተግባራዊነቱ ዓለም አቀፋዊ መሆኑ፣ የንግድ ሕግ በባሕሪው ተራማጅና ተቀያያሪ መሆኑ) ያሉት ከመሆኑ የተነሳ ከሌሎች የግለሰብ ሕጎች (Private Laws) ተለይቶ በአንድ ወጥ በሆነ መድብል (Code) መደራጀቱ የበለጠ ጠቀሜታ ይኖረዋል።የንግድ ሕጉ ተሰባስቦ በአንድ ወጥ መድበል መደራጀቱ በተለይ በንግድ ለመሰማራት ለሚፈልጉ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ነጋዴዎች የንግድ ሕጉን በቀላሉ ለመረዳት ከማስቻሉም በላይ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ የራሱ የሆነ ድርሻ ያበረክታል። በቀጣይ ለዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅት አባልነት ለምናደርገው ዝግጅትም የንግድ ሕጋችንን በተሟላ መልኩ መረዳት ስለሚያስችል በጎ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

በዚህ ዙሪያ የተለያዩ አገራት ልምድ ለመቃኘት ተሞክሯል። አንድ የሕግ መድብል ሲቀረጽ በተቻለ መጠን ምሉዕ ሆኖ መውጣት ስለሚኖርበት እንደ ኮሪያና ስፔይን የንግድ ሕጎች ለአገር ውስጥ ነጋዴውም ሆነ ለውጭ አገር ነጋዴ ይበልጥ ቀላል እና ተደራሽ መሆን እንዲችል የሚቀረፀው የአገራችን የንግድ ሕግ በአዋጅ የወጡ የተበታተኑ ሕጎችን፣ እንዲሁም የንግድ ባህሪ ያላቸውን ከፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ የሽያጭ ሕግ፣ የእንደራሴነት ሕግ፣ የኮሚሲዮን ሕግ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ማስያዣ (Mortgage) ሕግ፣ በአንድ ላይ ያካተተ ቢሆን ይመረጣል የሚለው አንድ ሐሳብ ሆኖ ቀርቧል።

ሌላውና ሁለተኛው አማራጭ ሐሳብ ከንግድ ሕጉ በኋላ በወጡ አዋጆች ውስጥ ያሉትን በማጠቃለል ነገር ግን የፍትሐብሔር ሕጉ ላይ ያሉትን ሳይጨምር በአንድ ላይ ይደራጅ የሚል ነው። በአገራችን የንግድ ሕግ ከግለሰብ ሕግ መድብል በተናጠል ራሱን በቻለ መድብል ምሉዕ ሆኖ መደራጀት አለበት ለሚለው ዋነኛ ምክንያቶች፡-

1) የአገራችን የወደፊት አቅጣጫ ከሲቪል ጉዳዮች ይልቅ የንግድ ጉዳዮች የሚበዙበት ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ምክንያቱም አሁን እርሻ ላይ የተመሠረተው ኢኮኖሚያችን ቀጣይ ወደ ኢንዱስትሪና ንግድ እየተሸጋገረ የሚሄድ በመሆኑ የንግድ እንቅስቃሴው እየሰፋና እየተጠናከረ የሚሄድ ይሆናል። ይህም ሁኔታ ከንግድ ሥራ ጋር ሙሉ አቅሙንና ጊዜውን የሚሠራ ተቋምና የሕግም ሆነ ሌሎች ተያያዥ ባለሙያን ይጠይቃል። የንግድ ሕጉ ቢያንስ ለቀጣይ 50 ዓመታት ያገለግላል ተብሎ በመገመት በቀጣይ 50 ዓመታት በአገራችን ሊመጡ የሚችሉ ለውጦችን በደንብ በማየት የንግድ ሕጉ አስቻይና ወጥ ሆኖ በተናጠል መድብል ሊደራጅ ይገባዋል።
2) የንግድ እንቅስቃሴ የራሱ የሆነ ልዩ ባሕሪያት ያሉት በመሆኑ፣ የንግድ ሥራን የሚደነግገው ሕግ ቀላል፣ ቀልጣፋ፣ ጥራቱን የጠበቀና ዘመናዊነትን የተላበሰ እንዲሆን ለማስቻል፣ መንግሥት በኢኮኖሚው በተመረጠ ሁኔታ ለሚኖረው ጣልቃ ገብነት አመቺ እንዲሆን የሚሉት ተደማሪ ምክንያቶች ናቸው።

ሆኖም ግን የንግድ ሕግ በተናጠል መደራጀት (Autonomy of Commercial Law) ከሌሎች በግለሰቦች ሕግ ውስጥ ከሚደነገጉት ጋር በምንም አይገናኝም ማለት ሳይሆን የንግድ ሕጉ ወደ ፍትሐብሔር ሕጉ የሚያመላክታቸው አጠቃላይና የወል የሆኑ (ለምሣሌ ስለሰዎች ችሎታ፣ ስለውል በአጠቃላይና የመሳሰሉት) ድንጋጌዎች ይኖራሉ።

የንግድ ሕጉ መደራጀት ያለበት ከንግድ ሕጉ በኋላ በወጡ አዋጆች ውስጥ ያሉትን በማጠቃለል የፍትሐብሔር ሕጉ ላይ ያሉትን ሳይጨምር በአንድ ላይ ይደራጅ የሚለው የተሻለ ሀሳብ ሆኖ ተመርጧል፤ ምክንያቱም፣ የሕግ ወጥነትን (Legal Integration) ይጠብቃል፣ ሕገ መንግሥታዊ የሕግ አወጣጥ ሥልጣንን መሠረት ያደርጋል፤ የተፈፃሚነት ወሰኑን ይጠብቃል።

### 6.2.1. መጽሐፍ አንድ

በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ያለውና በ1952 ዓ.ም የወጣው የንግድ ሕግ አንደኛ መጽሐፍ ስለነጋዴዎችና የንግድ መደብሮች ይደነግጋል። ይህ መጽሐፍ በአራት ንዑሳን ክፍሎች ተከፋፍሎ የተደራጀ ነው። ድንጋጌዎቹም በነጋዴዎች ላይ ተፈፃሚነት ስለሚኖራቸው ጠቅላላ ደንቦች፣ የነጋዴዎች ረዳቶችና ወኪሎች፣ ነጋዴዎች ሊይዟቸው ስለሚገቡ የሂሳብ መዛግብት፣ ስለ ንግድ ምዝገባ እና የንግድ መደብርን የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች ናቸው። ከተቀሩት የንግድ ሕጎችን መጻሐፍት በተለየ መልኩ ይህ መጽሐፍ የሚሸፍናቸው ጉዳዮች በተለያዩ አዋጆች በከፊል ተለውጠዋል ። ለምሳሌ የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አሰጣጥን በተመለከተ ከሰስት ዓመት በፊት የወጣው አዋጅ ቁጥር 980/2008ን እና በቅርቡ የወጣው የማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1150/2011ን፣ እንዲሁም በቅርቡ የፀደቀውን በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ ስለሚሰጥ የዋስትና መብት የሚደነግገውን አዋጅ ቁጥር 1147/2011ን መጥቀስ ይቻላል። ከዚህ አኳያ የረቂቁ መጽሐፍ አንዱ ዓላማ ተደርጎ የተወሰደው የንግድ ሕጉን ከእነዚህ በተለያዩ ጊዜያት ከወጡት ሕጎች ጋር የተጣጣመ፣ ተመጋጋቢ እና አላስፈላጊ ድግግሞሽ የሌለው ማድረግ ነው። በዚህም ምክንያት የመጽሐፍ አንድ ድንጋጌዎች ከአንቀጾች ብዛት አንጻር ሲታይ ቀንሷል።

ሆኖም ግን አሁን በሥራ ላይ ያሉት የአንደኛ መጽሐፍ አብዛኛዎቹ መርሆዎችና ደንጋጌዎች አንዳንድ መጠነኛ ማሻሻያዎችና የቋንቋ አርትኦት ተደርጎባቸው ባሉበት እንዲቀጥሉ ተደርገዋል። በመሆኑም በአጠቃላይ ሲታይ በአዲሱ ረቂቅ ውስጥ ከሁሉም ያነሰ ለውጥ የተደረገው መጽሐፍ አንድ ላይ ነው። በመሆኑም በመጽሐፍ አንድ ላይ ከተደረጉት ለውጦች ውስጥ መሰረታዊ የሆኑት  በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል።

#### ሀ) ስለ ነጋዴዎች ትርጓሜና የንግድ ሥራዎች ዝርዝር

የንግድ ሕጉ አንቀጽ 5 ነጋዴዎች ማለት የሙያ ሥራቸው አድርገው ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 21 ሥር የተዘረዘሩትን የንግድ ሥራዎች የሚሠሩ ናቸው ሲል ይተረጉማል። ይህ ዓይነቱ ትርጉም የተፃፈ የሕግ ሥርዓት ባላቸው አገሮች ዘንድ የተለመደ ነው። ለነጋዴ የተሰጠው ትርጓሜ ትክክል ቢሆንም ነጋዴው ሊሠራቸው የሚችላቸው የንግድ ሥራዎች ግን ዘርዝሮ ያበቃ (Exhaustive listing) ነው። ይህ ማለት በአንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ-አንቀጽ 21 ድረስ ከተዘረዘሩት ተግባራት ውጪ ያሉ ሌሎች ሥራዎች እንደ ንግድ ሥራ አይቆጠሩም ማለቱ ነው። አዳዲስ፣ ከዘመኑ ጋር የተከሰቱ ወይም ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ የንግድ ሥራዎችን መጨመር ወይም ማካተት አያስችልም። ይህ የራሱ ችግር ፈጥሯል። ለምሳሌ አዲስ ሀሳብ ይዞ የንግድ ምዝገባ የሚጠይቅ ሰው ሥራው በአንቀጽ 5 ሥር ተዘርዝሮ ያልተቀመጠ ስለሆነ በነጋዴነት ሊመዘገብ አይችልም። ይህ አሰራር አሳሪ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሰዎች አዳዲስ ሀሳቦችን እንዲያመነጩና ወደ ንግድ ሥራ ቀይረው የሞያ ተግባራቸው በማድረግ ጥቅም እንዲያገኙ አያበረታታም። በመሆኑም በረቂቁ ላይ በተመለከተው መልኩ አዳዲስ የንግድ ሥራዎች በተጨማሪነት ተዘርዝረው እንዲካተቱ የተደረገ ሲሆን ዝርዝሩም ጠቋሚ (Indicative Listing) እንዲሆን ተደርጓል። ይህም አሁን በረቂቁ ውስጥ ያልተካተቱ አዳዲስ ሀሳቦች ወደፊት ሲፈጠሩ የሕግ ማሻሻያ ማድረግ ሳያስፈልግ የንግድ ምዝገባ የሚያካሄደው አካል ነጋዴውን እንዲመዘግብ ያግዘዋል ማለት ነው።

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 6፣7፣ እና 8 መሠረት እንደ ነጋዴ የማይቆጠሩ ሰዎች ናቸው የተባሉትን በተመለከተም ማሻሻያ ተደርጓል። በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት የእርሻ ሥራ፣ የደን ማልማት ሥራ፣ ከብት የማርባት ሥራ የሚሠሩ የእርሻ ሰብላቸውን ወይም የከብቶታቸውን ርቢዎች የሚሸጡ፣ እንዲሁም ዓሣ አጥማጆች እና አርቢዎች ነጋዴዎች አይባሉም። ነገር

ግን እነዚህን ሥራዎች ለንግድ ዓላማና በንግድ መጠን (Commercial Purpose and Commercial Scale) የሚሠራ ሰው ነጋዴ የማይባልበት ምክንያት አይኖርም። ለምሳሌ ለኢንቨስትመንት በተሰጠው መሬት ላይ የእርሻ ወይም የደን ልማት ሥራ በመሥራት ምርቱን ለገበያ የሚያቀርብ ወይም በዚሁ መሬት ላይ እንስሳትን በማርባት ወይም በማደለብ ለገበያ የሚያቀርብ ሰው ነጋዴ ሊባል ይችላል። በእርግጥ ነጋዴ ሊባል የሚችለው እነዚህን የእርሻ ወይም የደን ልማት ሥራዎችን ከአነስተኛ መጠን በላይ የሚሠራ ሰው ከሆነ ነው ። «አነስተኛ መጠን» ማለት ምን ማለት እንደሆነ ደግሞ በረቂቁ አንቀጽ 6(2) ሥር ተመልክቷል።

### *ለ) ስለ ሒሳብ*

ነጋዴነት ከሚያስከትላቸው ግዴታዎች አንዱ የሒሳብ መዛግብት መያዝ ነው። የንግድ ሕጉ ከአንቀጽ 63 እስከ 85 ባሉት ድንጋጌዎች የሒሳብ መዝገብ አያያዝን በተመለከተ መሠረታዊ መርሆዎችንና ዝርዝር ደንቦችን አስቀምጧል። ዝርዝር የሒሳብ አያያዝ ደንቦችና ስሌቶች በሕጉ ውስጥ እንዲፃፉ የተደረገው በወቅቱ ዘመናዊ የንግድ ሥራና አሰራር በአገራችን ብዙም ያልተለመደ በመሆኑ እና ዘመናዊ የሒሳብ መዝገብ አያያዝ ትምህርትም ያልዳበረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ነጋዴውን ለማገዝ (ለማስተማር፣ ለመምራት) ያስችላል በሚል እሳቤ ነው። ይህ ዓይነቱ ሥጋት በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ ተወግዷል ማለት ባይቻልም ሕጉ ከወጣ ከ60 ዓመት በኃላ እና ዘመናዊ የሒሳብ አያያዝ ትምህርት እየተስፋፋ ባለበት ሁኔታ የቀደመው ሥጋት አሁንም እንደነበር ነው ማለት አይችልም። ከዚህ በተጨማሪም በሕጉ ላይ የተቀመጡት ዝርዝር የሒሳብ ደንቦች ከአዳዲስ ሃሳቦችና አሰራሮች ጋር የማይጣጣሙና ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ባለመሆናቸው የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 ወጥቶ በሥራ ላይ ውሏል። በመሆኑም የንግድ ሕጉ ዝርዝር ደንቦችን በመተው ከነጋዴው የሂሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታ ጋር አግባብነት ያላቸው መርሆዎች ላይ ብቻ እንዲያተኩር ተደርጓል። በዚሁ መሠረት በሚከተሉት የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ውስጥ የተካተቱት መሰረታዊ መርሆዎች ብቻ እንዲቆዩ ተደርጓል።

1ኛ) አንቀጽ 63፡- ማንኛውም ነጋዴ የሒሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታው ስለመሆኑ (የረቂቁ አንቀጽ 61) ፤

2ኛ) አንቀጽ 64፡- አነስተኛ ንግድ ሥራ የሚሠሩ ነጋዴዎች የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ የማይገደዱ መሆናቸው እና የአነስተኛ ንግድ ሥራ አሠራርና ካፒታል በሕግ እንደሚወሰን መሆኑ (የረቂቁ አንቀጽ 62) ፤

3ኛ) አንቀጽ 69 እና 70፡- የንግድ መዛግብት እንዲሁም ወጪና ገቢ ደብዳቤዎች ቢያንስ ለ10 ዓመት ተጠብቀው መቆየት ያለባቸው ስለመሆኑ (የረቂቁ አንቀጽ 66 እና 67) ፤

4ኛ) አንቀጽ 71 እና 72፡- የሒሳብ መዛግብት ስለነጋዴውም ሆነ በነጋዴው ላይ ማስረጃ መሆን መቻላቸው (የረቂቁ አንቀጽ 68 እና 69) ሆነው ቀጥለዋል።

የተቀሩት ድንጋጌዎች ማለትም አንቀጽ 66 (ስለ ዕለት ንግድ ምዝገባ) ፣ አንቀፅ 67 (ስለ ዕቃ መዝገብ እና የሒሳብ ማመዛዘኛ፤አንቀጽ 68 (ስለ መዛግብት አያያዝ ወይም ቅደም -ተከተል) እና ከአንቀጽ 73-85 ያሉ የሒሳብ አያያዝ ዝርዝር ደንቦች በሙሉ ከንግድ ሕጉ እንዲወጡ ተደርገዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የረቂቁ አንቀጽ 63 «ነጋዴዎች መያዝ ስለሚገባቸው

የሒሳብ መዝገቦችና ሰነዶች እንዲሁም ስለ ሒሳብ መዝገብ አያያዝ ደንቦች ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል» በማለት በንግድ ሕጉ ውስጥ ያልተካተቱ ነገሮች በሌላ አግባብነት ያለው ሕግ (አዋጅ ቁጥር 847/2006) እንደሚሸፈን አቅጣጫ አስቀምጧል። በመጨረሻም የሒሳብ መዝገቦችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መያዝ እንደሚቻል፣ በዚህ መልኩ ዓይነተኛ የሒሳብ መዝገቦች ማሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች፤ይህም ከተሟላ እንደማንኛውም የሒሳብ መዝገብ በሕግ ፊት ዋጋ ያላቸው መሆናቸው በረቂቅ አንቀጽ 65 ሥር ተመልክቷል።

### *ሐ) ስለ ንግድ ምዝገባ*

የሒሳብ መዝገብ ከመያዝ ሌላ ነጋዴነት የሚያስከትለው ዋናው እና የመጀመሪያው የሕግ ግዴታ ምዝገባ ነው። ማንኛውም ነጋዴ በንግድ መዝገብ ውስጥ በአግባቡ መመዝገብ ይኖርበታል። የንግድ ሕጉ ከአንቀጽ 86-123 ያሉ ድንጋጌዎች ይህንን ግዴታ ለማስፈጸም ዋና ዋና መርሆዎችን እና ዝርዝር ደንቦችን አስቀምጠዋል። ከዚህ በተጨማሪም ብዙ ጊዜ በመሻሻል የሚታወቀው የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አዋጅ እና የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ የዚህ የምዝገባ ሕግ አካል ናቸው። በንግድ ሕጉ እና በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መካከል ያለው አንድነት እና ልዩነት ግልጽ መደረግ አለበት።

የንግድ ምዝገባ መሠረታዊ ዓላማ ስለ ነጋዴው እና ስለ ንግዱ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ለሦስተኛ ወገኖች መግለጽ ነው። የንግድ መዝገቡም ለሕዝብ ክፍት ስለሚሆን ከነጋዴው ጋር መዋዋል የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በንግድ መዝገቡ ውስጥ የተመዘገቡትን መረጃዎች አስቀድሞ በመመልከት ተገቢውን ውሳኔ ለመወሰን ይችላል። እንግዲህ የንግድ ምዝገባ መሠረታዊ ዓላማ ይህ ከሆነ የንግድ ሕጉ ይዘት ይህንኑ ዓላማ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ፣ የጸኑ፣ በየጊዜው በቀላሉ በማይለዋወጡ መርሆዎች ላይ ብቻ መወሰን አለበት። የንግድ ምዝገባን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ተለዋዋጭነት ያላቸው ዝርዝር ድንጋጌዎች ግን ከንግድ ሕግ መውጣት አለባቸው።

በመሆኑም በንግድ ምዝገባና ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 እና በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1150/2011 ውስጥ ስለ ንግድ ምዝገባ የተደነገጉት መሰረታዊ መርሆዎች ተለይተው በንግድ ሕጉ ረቂቅ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርገዋል። የተቀሩት ዝርዝር የአፈጻጸም ድንጋጌዎች ግን ሊለዋወጡ ስለሚችሉ በንግድ ሕጉ ረቂቅ ውስጥ አልተካተቱም። ለጊዜው ባሉበት ሁኔታ በአዋጁ ውስጥ ይቀጥላሉ። እንደ አርቃቂዎቹ እይታ እነዚህ ተለዋዋጭነት ያላቸው ዝርዝር ድንጋጌዎች በአዋጅ ውስጥ ከሚቀጥሉ ይልቅ ወደፊት በምኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ውስጥ ቢጠቃለሉ የተሻለ ይሆናል።

ከንግድ ምዝገባ ጋር በተያያዘ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሌላው ነጥብ የንግድ ምዝገባ ሕግ እና የንግድ ፍቃድ ሕግ ዓላማቸውም ሆነ ባሕሪያቸው ለየቅል መሆናቸው ነው። የንግድ ፍቃድ ሕግ ቀጥተኛ ዓላማ አስተዳደራዊ ቁጥጥር ማድረግ ሲሆን የሚመደበውም ከአስተዳደር ሕግ (public/administrative law) ወገን በመሆኑ የግለሰቦችን ግንኙነት ከሚገዛው የምዝገባ ሕግ (private law) ጋር አንድ ላይ ተዳብሎ የሚወጣበት አመክንዮ የለም። ሥራ ላይ ያለው የ1952ቱ የንግድ ሕግ የንግድ ፈቃድ አሰጣጥ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ያላካተተው በዚህ ምክንያት ነው። በመሆኑም ረቂቁ የንግድ ሕግ የንግድ ፈቃድን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን አልያዘም። የፈቃድ ጉዳይ አሁን እንደሆነው ሁሉ በሌሎች ሕጎች መገዛቱ ይቀጥላል።

### *መ) ስለንግድ መደብር*

የንግድ ሕጋችን መጽሐፍ አንድ ስለንግድ መደብር (መድብል) የሚደነግጉ 85 አንቀጾች የያዘ መሆኑ ይታወቃል። ሕጉ ከ124 እስከ 209 ባሉት አንቀጾች ሥር ስለ ንግድ መደብር ትርጓሜ እና ይዘት፣ ሽያጭ፣ ኪራይ፣ ዋስትና፣ መዋጮ አድርጎ መስጠት ይደነግጋል። እንደሚታወቀው በተለያዩ ጊዜያት እነዚህ ድንጋጌዎች ላይ ለውጥ የሚያደርጉ አዋጆች ወጥተዋል። ለምሳሌ

የንግድ መደብርን የሚመለከቱ በአንቀጽ 135 እስከ 139 ሥር ያሉት የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ስለ ንግድ ስም በሚደነግጉት የአዋጅ ቁጥር 980/2008 ድንጋጌዎች ተሸፍነዋል። በንግድ መደብር ላይ ስለሚሰጥ ዋስትና የሚደነግጉት የንግድ ሕግ አንቀጽ 175፣178፣179፣181-186 እና 189 ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 1149/ 2008 ተለዋውጠዋል። ሌሎች የንግድ ምልክትን፣ አእምሮአዊ ንብረትን የተመለከቱት የንግድ ሕጎችም በልዩ ሕጎች ተተክተዋል። በመሆኑም ረቂቁ የንግድ ሕግ እነዚህ ጉዳዮችን የተመለከተቱት የመጽሐፍ አንድ ድንጋጌዎች በየጊዜው ከወጡት ሕጎች ጋር የተጣጣሙ እና ተመጋጋቢ እንዲሆኑ መጠነኛ ማሻሻያዎችን ያደርጋል።

### 6.2.2 መጽሐፍ ሁለት

## ሀ) አነስተኛ ድርሻ ላላቸው ባለአክሲዮኖች የሚደረግ ጥበቃ

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ኑሮው ከእጅ ወደ አፍ መሆኑ ይታወቃል። ሻል ያለ ደረጃ ላይ የሚገኙት ጥቂቶችም ቢሆኑ ትርጉም ያለው ተቀማጭ ገንዘብ የላቸውም ሊባል ይችላል። በመሆኑም አገራችን ሥራ ላይ ሊውል (ኢንቨስት ሊደርግ) የሚችል ካፒታል ከፍተኛ እጥረት አለባት። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚገኝ አገር ውስጥ እድገት ለማምጣት ዜጎች በተናጠል ያላቸውን እጅግ ውስን ሀብት አስተባብሮ ወደ ሥራ ማስገባት የግድ ይላል። ይህ እንዲሳካ ደግሞ ዜጎች የቆጠቡትን ትንሽ ገንዘብ በንግድ ማኅበር ውስጥ ካስገቡ በኋላ ለምዝበራ እና ጭቆና እንዳይዳረጉ የሚከላከል ሕግ መኖር አለበት።

አሁን ሥራ ላይ ያለው የንግድ ሕጋችን በኩባንያዎች ውስጥ አነስተኛ ድርሻ ይዘው የሚገቡትን ባለሃብቶች ከዘረፋ፣ ካልተገባ ጭቆና ወይም በደል ለመታደግ ያለሙ ድንጋጌዎች በበቂ ሁኔታ አላካተተም። በዚህም የተነሳ ኢኮኖሚው ያፈራውን አነስተኛ ካፒታል አሟጦ በተደራጀ መልክ ሥራ ላይ ማዋል አስቸጋሪ ሆኖ ተገኝቷል። አልፎ ተርፎም ይህ ክፍተት አገሮች ለንግድ ምን ያህል አመቺ እንደሆኑ በሚለካው በዓለም ባንክ የሚደረግ ምዘና ኢትዮጵያ በየዓመቱ በጣም ዝቅተኛ ውጤት እንድታገኝ አድርጓል። በዚህም የተነሳ አገራችን የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብ በምታደርገው ጥረት ላይ ዕንቅፋት ሆኖ ቆይቷል።

ስለዚህም ረቂቅ ሕጉ ይህን ሁኔታ ለመለወጥ እና አነስተኛ ድርሻ ያላቸውን የኩባንያ አባላት ከምዝበራ እና ኢፍትሃዊ አሰራር ለመጠበቅ የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን አካቷል። በዚህ ረገድ ረቂቅ ሕጉ ያደረጋቸው ለውጦች በሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው። እነዚህም፡-

1) <u>ግልጽነትን ማስፈን፡</u>- አንድ ኩባንያ ከኩባንያው ጋር ዝምድና ካላቸው ሌሎች ድርጅቶች ጋር ስለሚያደርጋቸው ውሎች አናሳ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች የተሟላ መረጃ እንዲያገኙ እና የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ የሚረዱ በርካታ ድንጋጌዎች በረቂቁ ውስጥ ተካተዋል። ለምሳሌ ያክል የረቂቅ ሕጉን አንቀጽ 323፣ 324፣ 325፣ 406፣ 392፣ 393፣ 396፣ 503 እና 504ን መጥቀስ ይቻላል።
2) <u>ተጠያቂነትን ማስፈን፡-</u> የንግድ ማኅበር ሥራ አመራር በተለይ የዳይሬክተሮችን ኃላፊነት በማያሻማ መልክ የሚያስቀምጡ እና ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑ አሰራሮችን ለመዘርጋት ያለሙ በርካታ ድንጋጌዎች በረቂቁ ውስጥ ተካተዋል። በዚህ ረገድ የረቂቁ አንቀጽ 308፣ 326፣ 327፣ 329፣ 339፣ 366(1)(2)፣ 367(2) 400 እና 406 ተጠቃሽ ናቸው።
3) <u>በሥራ አመራር ውስጥ የማኅበርተኞችን ተሳትፎ ማጎልበት</u>፡- ረቂቁ ማኅበርተኞች በንግድ ድርጅታቸው አመራር ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚረዱ በርካታ ድንጋጌዎችን አካቷል። በዚህ ረገድ የረቂቁን አንቀጽ 312(3)፣ 316፣ 354፣ 362፣405፣406፣453፣ 520 እና 529ን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። እያንዳንዱ የአክሲዮን ማኅበር ድረ-ገጽ

እንዲኖረው እና በድረ-ገጹም ላይ የማኅበርተኞችን ንቁ ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚረዱ መረጃዎች እንዲሰጥ የሚደነግጉት አንቀጽ 492-494 ይህን ያሳያሉ።

### *ለ) አዳዲስ የንግድ ማኅበር ዓይነቶች*

በንግድ ማሕበራት ሕግ ውስጥ ከተካተቱት የማኅበር ዓይነቶች ውስጥ የተወሰኑት ሕጉ ከወጣ ከስልሳ ዓመት በኋላ እንኳን ሲሰራባቸው አይታይም። ለምሳሌ ተራ የሽርክና ማኅብር በመባል የሚታወቀው እና በንግድ ሕጋችን አንጽ ከ227 እስከ 270 ባሉት ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው የንግድ ማኅበር በሥራ ላይ ውሎ አናገኘውም። የማሕበሩ ባህሪ እና ጠቃሚነትም ሲያወዛግብ ይታያል።

በመሆኑም ረቂቅ ሕጉ ይህንን የንግድ ማኅበር ዓይነት በማስወጣት በምትኩ ሁለት አዳዲስ የንግድ ማኅበር ዓይነቶችን አካቷል። ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር በመባል የሚታወቅ ነው። ይህ ዓይነቱ የሽርክና ማኅበር ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ሰዎች የሙያ ለሙያ ደጋፊ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት የሚያቋቁሙት ማኅበር ነው። ለምሳሌ የኦዲት፣ የሕግ እና መሰል አገልግሎቶች በሌላው የዓለም ክፍል የሚሰጡት በዋናነት በዚህ መልክ በተደራጀ ማኅበር ነው። በመሆኑም የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 221 እስከ 233 በዚህ ዓይነቱ ማኅበር ተደራጅተው መሥራት ለሚፈልጉ ይህን አዲስ አማራጭ በሕጋችን ውስጥ አካተዋል።

ሌላው በተቀረው ዓለም እየተለመደ የመጣው አዲስ አደረጃጀት ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት ነው። ይህ ማኅበር ኃላፊነቱ ከተወሰነ የግል ማኅበር (private limited company) ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው። ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ቢያንስ ሁለት አባላት እንዲኖሩት ሕጋችን ይደነግጋል። ያም ሆኖ ግን ብዙ ጊዜ ይህንን ድንጋጌ ለማሟላት ሲባል ብቻ ለይስሙላ እጅግ ትንሽ ብር ራሳቸው ከፍለው ሁለተኛ ሰው በማስገባት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የሚመሰርቱ ሰዎችን ማየት የተለመደ ነው። በሕጋችን መሰረት አሥር ብር ዋጋ ያለው አንድ አክሲዮን ብቻ የገዛ ሁለተኛ ሰው መግባቱ ይህ ዓይነቱን ማኅበር ለመመስረት በቂ ነው። ስለሆነም በተጨባጭ ምንም ዓይነት ትርጉም ያለው ገንዘብ ያላዋጣ፣ ከማሕበሩ ምንም ጥቅም የማያገኝ እና በማሕበሩ አመራርም ተጨባጭ ተሳትፎ ለማድረግ ምንም ፍላጎት የሌለው የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ ለይስሙላ ብቻ በማስገባት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር መመስረት ይቻላል። በተግባርም ይህ ሲሆን ይታያል። ይህ ከሚሆን ለብቻቸው ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ መመስረት ለሚፈልጉ ሰዎች አማራጭ በሕግ መዘርጋቱ ስለሚሻል ረቂቁ በአንቀጽ 534-545 ሥር ይህን አማራጭ አካቷል። ከዚህ ዓይነቱ ድርጅት ገንዘብ ለሚጠይቁ ሰዎች መደረግ ያለበትን ጥበቃ እና የድርጅቱን ሥራ አመራር የተመለከቱ የማሕበሩን ልዩ ባሕሪ ታሳቢ ያደረጉ ድንጋጌዎችንም ይዟል።

*ሐ) ተራ የሽርክና ማኅበር ከንግድ ሕጉ እንዲወጣ ማድረግ፣*

በንግድ ሕጉ ውስጥ ከተጠቀሱት የንግድ ማኅበራት አንዱ ተራ የሽርክና ማኅበር ነው። ይህ ማኅበር የሚቋቋምበት ዋና ዓላማ የንግድ ሥራ ለመሥራት አይደለም (አንቀጽ 213(1)። የንግድ ሥራ ለመሥራት ወይም ዓይነቱ ሳይገለጽ የሚቋቋም ከሆነ እንደ ሕብረት ሽርክና ማኅበር እንደሚቆጠር በአንቀጽ 213 ንኡስ (2) ተደንግጓል። በተለይ በሌሎች ዓይነት የንግድ ማኅበራት ሊከናወን የማይችል የጋራ የሆነ ሀብትን ለማስተዳደር ሲባል እንደሚቋቋም ከአንቀጽ 228 ንኡስ ቁጥር 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል። ይህም የሚያሳየው ተራ የሽርክና ማኅበር እንደሌሎቹ የንግድ ማኅበራት በራሱ ቅርጽ ቆሞ የንግድ ሥራ መሥራት የማይችል መሆኑን ነው።

በአገራችን ዓላማቸው የንግድ ሥራ መሥራት ያልሆኑ ማኅበራት የሚተዳደሩበት ልዩ ሕግ ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል። ሌሎችም በፍትሐብሔር ሕጉ የሚሸፈኑ አሉ። ከዚህ አኳያ ሲታይ የንግድ ማኅበራትን አሠራር ለመወሰን የወጣ ሕግ የንግድ ማኅበር ያልሆኑና በሌላ ሕግ የተሸፈኑትን በውስጡ እንዲካተት ማድረጉ ከልዩ ሕጉ ጋር ያለመጣጣም እንዲከሰት የሚያደርግና የንግድ ማኅበራት ሕጉ ከወሰነው ውጭ እንዲሆን አድርጓል።

ይህን አሠራር በሚመለከት ሶስት ዓይነት ልምዶች ከተለያዩ አገራት ተወስደዋል። ለተሞክሮ ከተወሰደባቸው አገራት ውስጥ አንዳንዶቹ የንግድ ሥራ የማይሰሩ የበጎ አድራጎትና ሲቪክ ማኅበራትንም በኩባንያ ሕጋቸው የሚያካትቱበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ፡- የእንግሊዝ የኩባንያ ሕግ (እ.አ.አ. 2006) ክፍል 3-6 እና የደቡብ አፍሪካ ኩባንያ ሕግ (እ.አ.አ.2008) ክፍል 8 ለአብነት ይጠቀሳል። እነዚህ አገራት የበጎ አድራጎትና ሲቪል ማኅበራትን የሚያስተዳድሩበት የተለየ ሕግ የላቸውም። ሌሎቹ ደግሞ በንግድ ሕጋቸው ውስጥ የሚያካትቱት ለንግድ ሥራ የሚቋቋሙ ማኅበራትን ብቻ ነው። ለምሳሌ ያህል በፈረንሳይ ንግድ ሕግ አንቀጽ L210-1 እና በደቡብ ኮርያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 170 ላይ በግልጽ የህብረት ሽርክና፣ ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት ሽርክና፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የሕዝብ ኩባንያ የተቋቋሙት ዓላማ ምንም ይሁን ምን በመቋቋማቸው ብቻ የንግድ ሥራ እንደሚሠሩ ሕጉ ግምት ይወስዳል። በጀርመን ደግሞ የንግድ ሥራ የሚሠሩ የሽርክና ማኅበራት ዓመታዊ የገንዘብ ዝውውራቸው ወይም ዓመታዊ ትርፋቸው ከተወሰነ የገንዘብ መጠን በታች ከሆነ የሚተዳደሩት በንግድ ሕግ ሳይሆን በፍትሐብሔር ሕግ ነው (የጀርመን የፍትሐብሔር ሕግ ክፍል 705/704(BGB)። እንደነዚህ ዓይነት ማኅበራት Civil Law Partnership ወይም በጀርመን GbR ተብለው ይጠራሉ።

በአገራችን የንግድ ማኅበር ያልሆኑ ማኅበራትን የሚያስተዳድሩ ሌሎች ሕጎች ከመኖራቸው አንፃር የንግድ ኩባንያ ያልሆነውን አደረጃጀት ንግድ ሕጉ ውስጥ ማካተቱ የአሠራር መዘበራረቅ የሚያስከትል በመሆኑ ተራ የሽርክና ማኅበር ከንግድ ሕጉ እንዲወጣ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ረቂቁ በዚሁ መልኩ ተዘጋጅቷል።

*መ) የኩባንያዎች መቧደን*

በተለያዩ ምክንያቶች እና ዘዴዎች ኩባንያዎች መሃል ዝምድና ሊፈጠር ይችላል። ለምሳሌ የአንድ ቤተሰብ አባላት ሁለት ኩባንያዎች ውስጥ ወሳኝ ድርሻ ሊኖራቸው ወይም ጭራሽ የኩባንያዎቹን አክሲዮኖች ሙሉ በሙሉ ሊይዙ ይችላሉ። በተመሳሳይ አንድ ኩባንያ ብዙ ኩባንያዎች ውስጥ ወሳኝ የሆነ የአክሲዮን ድርሻ ሊኖረው ይችላል። በሌላ በኩል ድግሞ ሁለት ኩባንያዎች እርስ በርስ አንዱ በሌላኛው አክሲዮን ሊኖራቸው ይችላል። በዚህ መልኩ የኩባንያዎች እህትማማችነት በአገራችንም እየተለመደ መጥቷል።

የኩባንያዎች ዝምድና አስፈላጊው ሕጋዊ ማዕቀፍ ካልተዘረጋለት በተለያዩ ሰዎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። ለምሳሌ ዝምድና ባላቸው ኩባንያዎች መካከል የሚደረጉ ውሎች ሆን ተብለው የአንዱን ኩባንያ ገንዘብ ጠያቂዎች በሚጎዳ መልክ

ሊደረጉ ወይም ሊተገበሩ ይችላሉ። በተጨማሪም የሁለቱ ኩባንያዎች ግንኙነት በኩባንያዎቹ ውስጥ አናሳ ድርሻ ባላቸው ባለአክሲዮኖች ላይ ጉዳት የሚያደርስበት ሁኔታ አለ። ሆኖም የንግድ ሕጋችን እንዲህ ዓይነቱን የኩባንያዎች መቧደን ወይም ዝምድና የሚመለከት አንድ አንቀጽ ብቻ ነው ያለው። ይህን ጉዳይ የሚመለከተው አንቀጽ 344 አንዱ የአክሲዮን ማኅበር የሌላ ማኅበር ካፒታል አሥር በመቶ የያዘ ከሆነ ሁለተኛው ማኅበር በአንደኛው ውስጥ አክሲዮኖች ሊኖሩት እንደማይችል በመደንገግ የተወሰነ ነው።

በመሆኑም ረቂቁ ሕግ የኩባንያዎች መቧደን ሊያስከትል የሚችላቸውን የተለያዩ ችግሮች ለመከላከል የሚረዱ አሥራ አራት አንቀጾችን አካቶአል። ለዝርዝሩ በረቂቁ አንቀጽ 550-564 ሥር ያሉትን ድንጋጌዎች ማየት ይቻላል።

*ሠ) የኩባንያዎች መዋሃድ እና መከፋፈል*

ሌላው የንግድ ሕጋችን ክፍተት የኩባንያዎች መዋሃድ እና መከፈልን በተመለከተ ነው። በተለይ አንድ ኩባንያ ለሁለት ወይም ከዛም በላይ ሲከፈል በድርጅቱ ገንዘብ ጠያቂዎች እና በዚህ ውሳኔ በማይስማሙ ባለአክሲዮኖች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል የሚረዳ አንድም ድንጋጌ አላካተተም። በአንጻሩ ከአንቀጽ 544 እስከ 554 ያሉት የንግድ ሕጋችን ድንጋጌዎች ስለመዋሀድ የሚደነግጉ ቢሆንም ከማሕበራት መለወጥ ጋር አንድ ላይ ነው፣ የተሟሉም አይደሉም። ረቂቅ ሕጉ በዚህ ረገድ ሕጋችን ያለበትን ክፍተት ለመድፈን በአንቀጽ 565-577 ሥር ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካቷል።

*ረ) በውጭ አገር ስለተቋቋመ ማኅበር ቅርንጫፍ*

በውጭ አገር የተቋቋመ የንግድ ማኅበር ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ከፍቶ ሊሰራ እንደሚችል ይታወቃል። የንግድ ሕጋችን ስለዚህ ጉዳይ ምንም አይናገርም። የኢንቨስትመንት እና የንግድ ምዝገባ አዋጆች ግን ይህ ሊሆን እንደሚችል ያመላክታሉ። ሆኖም የውጭ አገር የንግድ ማኅበር ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ከፍቶ በሚሰራበት ጊዜ ከቅርንጫፉ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያለቸው ሰዎችን ከጉዳት ለመጠበቅ የሚረዱ ዝርዝር ድንጋጌዎች በሕጋችን ውስጥ የሉም። ስለዚህ ረቂቅ ሕጉ ከቅርንጫፉ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያላቸውን ሰዎች መብት ከጉዳት ለመታደግ የሚረዱ ድንጋጌዎችን በአንቀጽ 578-583 ሥር አካቷል።

በአጠቃላይ መጽሐፍ ሁለት ሥር የተደረጉት ለውጦች ከላይ የተገለጹት ብቻ አይደሉም። ሆኖም ረቂቅ ሕጉ ያደረጋቸውን ለውጦች ዓይነት እና መጠን  አመላካች የሆኑ አንኳር ለውጦች ከላይ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

## 6.2.3 መጽሐፍ ሦስት/ በነባሩ መጸሀፍ አምስት የነበረ/

በ1952 የወጣው የንግድ ሕግ በሶስተኛው መጽሐፍ ሥር የሚደነግገው በየብስ እና በአየር ስለሚደረግ የማጓጓዝ ሥራ፣ የመድን ሥራ እንዲሁም ስለውርርዶች እና ኪሳራ ጨዋታ (games and gambling) ነው። በአንጻሩ የንግድ ሕጋችን አምስተኛውና የመጨረሻው መጽሀፍ ደግሞ አንድ የንግድ ድርጅት ኪሳራ ሲገጥመው ከተቻለ ድርጅቱን ለማትረፍ ካልተቻለም የተገኘውን ያክል ንብረት ከብክነት በመታደግ ለገንዘብ ጠያቂዎች በፍትሐዊ መንገድ ለማከፋፈል ስለሚቻልበት ሁኔታ የሚደነግጉ የኪሳራ እና የመጠባበቂያ ስምምነትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ያካትታል። ረቂቁ የንግድ ሕግ መጽሐፍ አምስትን ሦስተኛ መጽሐፍ አድርጓል። የንግድ ሕጋችን መጽሐፍ ሦስት እና አራት ደግሞ የፋይናንስ አገልግሎቶች ኮድ ተብለው ተሰፋፍተው በሌላ ኮድ እንዲወጡ መወሰኑ እና ለዚህ ውሳኔ መነሻ የሆኑ ዝርዝር ምክንያቶች ከላይ ተዘርዝረው ቀርበዋል።

የረቂቅ ሕጉ መጽሐፍ ሦስት ያካተታቸውን ጉዳዮች ስንመለከት መጽሐፉ ሰባት ርዕሶች ሲኖሩት በአጠቃላይ ሁለት መቶ ሰላሳ ስምንት (238) አንቀፆችን ይዟል። በዚህ የመድብሉ ክፍል የተካተቱ ዋና ዋና ለውጦችም የሚከተሉት ናቸው።

### *ሀ) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት (Preventive Restructuring)*

ይህ ሥነ ሥርዓት ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ሕጎች ውስጥ ተካቶ የማይታወቅ ሲሆን መሉ በሙሉ በአዲስነት በረቂቁ ውስጥ እንዲካተት የተደረገ ነው። ይህ የቅድመ ጥንቃቄ ሥነ ሥርዓት በሌሎች አገራት (ለምሳሌ በፈረንሳይ) ተቀባይነት አግኝቶ ውጤታማነቱ የተረጋገጠ ሲሆን የአውሮፓ ኅብረትም ይህን ጠቀሜታውን በመረዳት በህብረቱ የጋራ ሥርዓት እንዲሆን በቅርቡ መመሪያ አውጥቷል።

የዚህ ሥርዓት ዋና ዋና ባህርያት የሚከተሉት ናቸው:-

1. የፋይናንስና የኢኮኖሚ እክል ስላጋጠማቸው ዕዳቸውን ለመክፈል የማይችሉ የንግድ ተቋማት መደበኛ የንግድ ሥራቸውን እያከናወኑ ዋና ዋና ከሆኑ ገንዘብ ጠያቂዎቻቸው (ለምሳሌ ከባንኮች፤ አቅራቢዎቻቸውና ተቀባዮቻቸው) ጋር ዕዳቸውን በሚስጥር እንዲያደራጁ ዕድል ይከፍትላቸዋል።
2. ዕዳን በማዋቀር ሂደት ከሚሳተፉት ገንዘብ ጠያቂዎቻቸው በስተቀር ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች (ለምሳሌ ሰራተኞች) ሥርዓቱ ስለማይመለከታቸው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ያለምንም መስተጓጎል እንዲቀጥል ይረዳል።
3. ይህ ሥርዓት በሕግ በተወሰነ ጊዜ እንዲጠናቀቅ ህጉ ስለሚያስገድደው ባለዕዳዎች ዕዳቸውን በጊዜው እንዳይከፍሉ እንዳይገፉፉ ያደርጋል።
4. ይህ ሥርዓት በፍ/ቤት የሚፅድቀው ሁሉም በሥነ-ሥርዓቱ የተካተቱት ዋና ዋና ገንዘብ ጠያቂዎች ሙሉ በሙሉ የተስማሙበት ከሆነ ብቻ ስለሆነ ገንዘብ ጠያቂዎች ላይ ያለፈቃዳቸው ምንም አይነት ግዴታ አይጥልም።
5. የማዋቀር ሂደቱ ሙሉ በሙሉ በሚስጥር እንዲያዝ ህጉ ስለሚያስገድድ ባለዕዳዎች ያለምንም መሸማቀቅ በሥነ-ሥርዓቱ እንዲሳተፉ ያበረታታል።
6. በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ባለዕዳዎች የዕዳቸው ሁኔታ ከመባባሱ በፊት ቀድመው በሥነ-ሥርዓቱ እንዲጠቀሙ ስለሚያደርግ የንግድ ተቋማት ዕዳቸውን እንደገና በማደራጀት ከኪሳራ እራሳቸውን እንዲከላከሉ ይረዳል።

### *ለ) ዕዳን መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት (Reorganization)*

ሌላው እና ዋነኛው በረቂቁ የተካተተው ነገር መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ነው። መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት በንግድ እንቅስቃሴያቸው ለመቀጠል ተስፋ ያላቸው ነገር ግን ዕዳቸውን ለመክፈል እክል የገጠማቸው የንግድ ተቋማት ከገንዘብ ጠያቂዎች እና ከፍ/ቤት ጋር በመሆን ዕዳቸውን መልሰው የሚያደራጁበትና የሚያገግሙበት ሥነ-ሥርዓት ነው።

በተግባር ብዙም ተተግብሮ ባይታወቅም መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት በ1952ቱ የንግድ ሕግ እራሱን ችሎ የመጠበቅያ ስምምነት (schemes of arrangement) በሚል ተቀምጦ ይገኛል። አዲሱ ረቂቅ በ1952 የንግድ ሕግ ውስጥ የሚገኘውን የመጠበቅያ ስምምነት (schemes of arrangement) አንዳንድ መሰረታዊ ሃሳቦችን ተቀብሎ ወስዷል። በዚህ ረገድ ሌሎች አገራት የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት የረቂቁ ርዕስ 3 ሆኖ በአዲስና በዘመነ መልክ ቀርቧል። ርዕስ 3 ስልሳ ዘጠኝ (69) አንቀፆች ሲኖሩት በ 9 ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው።

### *ሐ) የኪሳራ ሥነ -ሥርዓት*

በሥራ ላይ ባለው የ1952ቱ የንግድ ሕግ በርዕስ ሁለት ሥር የተቀመጠና በተግባር ደግሞ የከሰሩ የንግድ ተቋማት ብቸኛ አማራጭ ተደረጎ ሲተገበር ቆይቷል - የኪሳራ ሥነ-ሥርዓት (bankruptcy)። አሁን ባለው ዘመናዊ አመለካከት በኪሳራ ምክንያት የንግድ ድርጅትን መዝጋትና ንብረቱን ሸጦ ለገንዘብ ጠያቂዎች ማከፋፈል የመጨረሻ እንጂ የመጀመርያ አማራጭ አይደለም። በመሆኑም ይህ ዘመናዊውን አመለካከት በረቂቁ ውስጥ የኪሳራ ሥነ ሥርዓት ከዋና ዋናዎቹ የመፅሀፍ 3 ሥነ ሥርዓቶች መጨረሻ አማራጭ ተደርጎ በመፅሀፉ ርዕስ 4 ሥር እንዲቀመጥ ተደረጓል። በዚህም መሰረት የቅድመ ጥንቃቄን የዕዳ ማደራጀት ሥርዓት ቀጥሎም ዕዳን እንደገና የማደራጀት ሥርዓት መጠቀም የማይችሉ እና ሌላ ብዙም አማራጭ የሌላቸው ድርጅቶች የኪሳራ ሥነ-ሥርዓት ውስጥ ይገባሉ። የዚህ ሥነ-ሥርዓት ዓላማ የድርጅቱን ቀሪ ሃብት ከብክነት በማዳን በፍትሃዊ መንገድ ለንዘብ ጠያቂዎች ማከፋፈል እና ባለዕዳውን ከንግድ ዘርፉ በሥርዓት ማስወጣት ነው።

### *መ. የከሰረን ሰው ነፃ ስለመደረግ (Discharge)*

የንግድ ህጋችን ከሚተችባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ በንፁህ ልቦና የሚከስሩ ነጋዴዎች ከዕዳ ነፃ የሚወጡበት የሕግ ድንጋጌ አለማካተቱ ነው። በዚህም ምክንያት ብዙ ነጋዴዎች የኪሳራን ሥነ-ሥርዓት ፈቅደው እንዳያመለክቱና የኪሳራ ሁኔታዎች እንዲባባሱ አድርጎዋል የሚል ሃሳብ አለ። ብዙ ዘመናዊ የሆኑ የኪሳራ ሕጎች ንፁህ ነጋዴዎች በተወሰነ መልኩ የኪሳራ ሥነ-ሥርዓቱ ከተዘጋ በኋላ ነጻ የሚሆኑበትን ሁኔታ ይደነግጋሉ።

አርቃቂ ቡድኑም ይህንን ዘመናዊ የኪሳራ ሕግ አመለካከት በሚያንፀባርቅ መልኩ ንፁህ ነጋዴዎች የኪሳራ ሥነ-ሥርዓቱ በሕጉ መሰረት ካበቃ በኋላ ከዕዳ ነፃ የሚሆኑባቸውን የሕግ ድንጋጌዎች በመፅሐፍ ሦስት በርዕስ 5 ሥር አስቀምጧል። በዚህም መሰረት አንድ የኪሳራ ውሳኔ የተላላፈበት ነጋዴ የኪሳራው ብይን ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ከሶስት ዓመት በኋላ ከዕዳ ነፃ ለመሆን ለፍ/ቤት ማመልከት እንደሚችል በረቂቁ ተካቷል።

ይህ መብት በዘፈቀደ ለሁሉም የሚሰጥ አይደለም። ንጹህ የሆኑ የተፈጥሮ ሰው ነጋዴዎችን ብቻ የሚመለከት ነው። እንደዚህም ሆኖ ከኪሳራ ጋር ተያያዠነት ያላቸውን ወንጀሎች ፈፅሞ የተፈረደበት፤ ንብረት ስለመደበቁ ወይም ማሸሹ ማስረጃ የቀረበበት፤ በኪሳራ ሥነ-ሥርዓት ሂደት ያልተባበረ ወይም ግዴታውን ያልተወጣ ነጋዴ ወይም ተደጋጋሚ የኪሳራ ውሳኔ በአምስት ዓመት ውስጥ ያስተናገደ ነጋዴ ይህን መብት አያገኝም። ከዕዳ ነፃ አይደረግም። በተጨማሪም የተወሰኑ ዕዳዎች ሌሎች ሕጎች በልዩ ሁኔታ ካልፈቀዱ በስተቀር ነፃ እንደማይደረጉ በረቂቁ ተካቷል።

### *መ) ቀላል የኪሳራ ሥነ-ሥርዓት ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች*

የመጨረሻው የመጽሐፍ ሦስት ርዕስ ቀላል የኪሳራ ሥነ-ሥርዓት ነው። ይህ የተቃለለ ሥነ-ሥርዓት የታሰበው ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ሲሆን ዓላማውም ሥነ-ሥርዓቱን ቀላል፤ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ በማድረግ ለኪሳራ የተዳረጉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በሥነ-ሥርዓቱ ከንግድ ሥርዓቱ የሚወጡበትን ሥርዓት መዘርጋት ነው።

ቀላል የኪሳራ ሥነ-ሥርዓት ሊከፍቱ የሚችሉት አነስተኛና መካከላኛ ኢንተርፕራይዞች ሲሆኑ እነሱም የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያማሉ ከሆነ ነው:-

1) ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት የሒሳብ ሚዛናቸው የሀብት መጠን ከ 20 ሚሊዮን ብር ያነሰ ከሆነ፤
2) የሠራተኛ ቁጥራቸው ከ 10 ያነሰ ከሆነ፤ ወይም
3) ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት ዓመታዊ ሽያጫቸው ከ 5 ሚሊዮን ብር ያነሰ ከሆነ ነው።

ይህን ሥነ-ሥርዓት ቀላል የሚያሰኙት ዋና ዋና ባህርያት የሚከተሉት ናቸው፡-

1) የሚቀርቡት ሰነዶችና አባሪዎች ዝርዝር አጭር መሆናቸው፤
2) በፍ/ቤቱ ተቆጣጣሪነትና በንብረት ጠባቂው ኃላፊነት ብቻ (ተቆጣጣሪ ዳኛና የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ ሳያስፈልግ) ሥነ-ሥርዓቱን ማከናወን መቻሉ፤
3) የንብረት ማጣራትና መሸጥ ተግባራት የተንዛዛውን መደበኛ ሥነ-ሥርዓቶች የግድ አለመከተላቸው፤
4) ንብረት ጠባቂው የባለዕዳውን ንብረት አጣርቶ፤ ሸጦ በአንድ ዓመት ውስጥ የማከፋፈል ግዴታ የተጣለበት መሆኑና ሥነ-ሥርዓቱም በአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ የታጠረ መሆኑ፤ እና
5) በዚህ ሥነ-ሥርዓት ሥር አልፈው ፋይላቸው የተዘጋላቸው የተፈጥሮ ሰዎች ከዕዳ ነፃ ወዲያውኑ ሊታወጅላቸው መቻሉ፤ናቸው።

ፍ/ቤቱም ቀላል የኪሳራ ሥነ-ሥርዓት ከተከፈተ ባንድ ዓመት ውስጥ መጠናቀቁን ማረጋገጥ ይኖርበታል።